

ማርያም ቤተ ክርስቲያን

# ትንሣኤ



በሰሜን የሚገኘው መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን

መጋቢት ፲፱፻፷፱ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ፤ ሥርዓትና ዜና፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »

ዋና አዘጋጅ ቀ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ
ም/ አዘጋጅ መ/ ክንፈ ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማውጫ

ገጽ

## አርእስት

ደብዳቤዎች ........................................ ፩
ርእሰ አንቀጽ (በፍቅራችን ፍርሃት አይኑር) ........................ ፪
እግዚአብሔር ከአንች ጋር ነው ........................................ ፬
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........................................ ፮
አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ........................................ ፯
፴ ዓመታት ሙሉ የሐዲስ ጉባኤ ዘርግተው የሚያስተምሩ መምህር ብርሃኑ ወልደ ሥላሴ ........................................ ፱
ሌሊት በመማር ቀን በማስተማር ........................................ ፲
የጩንቻ ማሠልጠኛ ፺፪ ካህናትን አስመረቀ ........................................ ፲፪
ክርስቲያናዊ ሕይወት ........................................ ፲፫
ዜና ሊቃውንት ........................................ ፲፭
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........................................ ፲፮
የትንቢትና ምሳሌዎች ትርጉም ........................................ ፲፯
የቅኔ አዝመራ ይሰብሰብ በወቅቱ ........................................ ፲፰
ዓቢይ ጾም ........................................ ፲፱
የደረሞ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ተፈጽሞ ታቦቱ ገባ ፳
ስብከተ ወንጌል ........................................ ፳፩
ከእንግዲህ የኃጢአት ዕዳ የለብንም ........................................ ፳፪
ከቋጥኝ ድንጋይ ተፈልፍላ የታነፀችው የደብረ ሲና ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........................................ ፳፫

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ስም የአክብሮት ምስጋናዬን አቀርባለሁ በነሐሴ ወር ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ባወጣችሁት በትንሣኤ መጽሔት እትማችሁ ዲያቆን ሞገስ አየለ ካቀረባቸው ጥያቄዎች ውስጥ በተራ ቁጥር ፪ ላይ የተዘረዘሩት አሳቦች በእኔም ልቡና ሲጉላሉ የቆዩ ስለነበር ለዲያቆን በተሰጠው መልስ ስለረካሁ በጣም አመሰግናለሁ ቀጥዬም ጥያቄ አቀርባለሁ ።

፩ኛ/ በቅዳሴ ጊዜ የግል ጸሎት መጸለይ እንደማይገባ እየታወቀ የጸሎት መጸሕፍት በብዛት እየታተሙ ለምን ይሸጣሉ?

፪ኛ/ እነዚህ የጸሎት መጻሕፍት የትእንደሚታተሙ በትንሣኤ መጽሔት ብትገልጹልኝ አመሰግናለሁ ።

ሲዳሞ ሀ/ስብከት አሬሮ አውራጃ ሀገረ
ማርያም ከተማ ታፈሰ ውድነህ ።

መልስ አቶ ታፈሰ ውድነህ ስለአቀረቡልን መንፈሳዊ ሰላምታ እያመሰገን ለጥያቄዎችም መልስ እንሰጣለን ።

በመጀመሪያው ጥያቄ በቅዳሴ ጊዜ የግል ጸሎት መጸለይ ተገቢ አለመሆኑ እየታወቀ የጸሎት መጻሕፍት ለምን በብዛት ይታተማሉ ስላሉት መጻሕፍቱ የሚታተሙት በቅዳሴ ጊዜ እንዲጸለዩ ሳይሆን ከቅዳሴ በፊትም ሆነ ከቅዳሴ በኋላ እንዲጸለይባቸው ነው እንጂ በቅዳሴ ጊዜ እንዲጸልይባቸው አይደለም ታዲያ በቅዳሴ ጊዜ ካልተጸለየባቸው ለምን ይታተማሉ የሚል አስተሳሰብ ሊኖር አይገባም በቅዳሴ ጊዜ ግን ከልኡካኑ ጋር ተሰጥወውን እየተቀበሉ አብሮ ከመጸለይ በስተቀር የግል ጸሎት መጸለይ በጥብቅ የተከለከለ ነው ።

እነዚህ የጸሎት መጻሕፍትም የሚታተሙት በሊቃውንት ታርመው በማሳተሚያ ድርጅት ተከታታይነት በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት በጥንቃቄ ታትመው ለምእመናኑ የሚቀርቡ ሲሆን ለንግድ ሲሉ ብዙ ጥንቃቄ ሳይደረግባቸው የሚያሳትሙ ክፍሎች አሉ ግን እርስዎም መጻሕፍቱን ከገዙ በኋላ በቅዳሴ ጊዜ እንዳይጸልዩ ይጠንቀቁ በቅዳሴ ጊዜ ጸሎት የተከለከለ ነውና ።

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
የትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ በክርስቶስ ስም አምነው ለተጠመቁትና ያላመኑትንም በትምህርተ ወንጌል ለማሳመን ለተመረጣችሁ ለሰባክያነ ወንጌል ከእግዚአብሔር አባታችን ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ እያልኩ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትሕትና አቀርባለሁ ።

፩ኛ/ አንዳንድ ምእመናን ዘወትር እሁድና በበዓላት ቀናት አስቀድሰው ጸበል ጠጥተው የመመለስ እንጂ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም የመቀበል ፍላጐት ያላቸው መስለው አይታዩም ይህ ተገቢ ነውን ?

፪ኛ/ ለአቅመ አዳም የደረሰ ክርስቲያን ሚስት ሳያገባ የክርስቶስን ሥጋና ደም መቀበል ይገባዋልን?

፫ኛ/ ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት አሉ እንስሳም አሏቸው ሰው ባያቸው ጊዜ ግን ወደ ባሕር ይገባሉ ይባላል ይህ እውነት ነውን?

፬ኛ/ ያላመነ ያልተጠመቀ ሰው በሞተ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ጸሎት ፍትሐት ሊደረግለትና በዐፀደ ቤተ ክርስቲያን መቀበር ይገባዋል? አዲስ በላይ

አዲስ በላይ ስላቀረብክልን ሰላምታ እያመሰገን ለጥያቄዎችህ መልስ እንሰጣለን፦

አንዳንድ ሰዎች ጸበል መጠጣት እንጂ ሥጋውንና ደሙን የመቀበል ፍላጐት የላቸውም ስለላከው አንተን ብቻ ሳይሆን ጉዳዩ እኛንም አስገርሞናል በየአብያተ ክርስቲያኑ ሥጋውንና ደሙን የሚቀበሉ ምእመናን በጣም አነስተኛ ሲሆኑ ጸበል ፈላጊው ግን ሁሉም ነው ግን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ ይኖራል አይሞትም ብሎ አስተማረን እንጅ የቅዳሴ ጸበል የጠጣ ለዘለዓለም አይሞትም ብሎ አላስተማረንም ስለዚህ ምእመናኑ የቅዳሴ ጸበል ለመጠጣት የሚሽቀዳደሙትን ያህል በሕግ እየተወሰኑ ኃጢአታቸውን ለንስሐ አባታቸው እየተናዘዙ ሥጋውንና ደሙን ቢቀበሉ የዘለዓለም ሕይወትን የሚያገኙ መሆናቸውን ሊያውቁትና ሊረዱት ይገባል የቅዳሴ ጸበል በመጠጣት ብቻ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት አይቻልምና ።

ሁለተኛው ጥያቄህ ለአቅመ አዳም የደረሰ ወንድ ሳያገባ ሥጋውንና ደሙን መቀበል ይገባዋልን የሚል ነው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም መቀበል በዕድሜ የሚወሰን አይደለም ንጹሕ ከሆነ ለአቅመ አዳም ደርሷልና ሥጋውንና ደሙን መቀበል አይገባውም ተብሎ አይከለከልም ይቀበላል ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ "ሰው ግን ራሱን ይፈትን እንዲሁም ከኅብስቱ ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍዳ ይበላልና ይጠጣልምና" በማለት ማንኛውም ሰው ከኃጢአት ነጽቶ ሥጋውንና ደሙን መቀበል እንዳለበት ተናግሯል ፩ኛ/ ቆሮ ፲፩.፳፰ ስለዚህ ከኃጢአት ንጹሕ የሆነ ሁሉ ሥጋውንና ደሙን ከመቀበል የሚከለክለው የሌለ አለመኖሩን በመግለጽ መልሳችን እናጠቃልላለን ።

ሶስተኛ ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት አሉ እንስሳም አሏቸው ሰው ባያቸው ጊዜ ግን ወደ ባሕር ይገባሉ ይባላል ይህ እውነት ነውን ስትል ያቀረብከው ጥያቄ እውነትን ያልያዘ ነው በእርግጥ አንተ እንዳልከው የሚነገር የአፍ ታሪክ አለ እንጂ የተጻፈ ታሪክ አላገኘንም ግን ሰውን በሚያሳስቱበት ጊዜ ልቡሳነ

ተከታዩን በገጽ ፭ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# በፍቅራችን ፍርሃት አይኑር

ለፍቅር የተለያዩ መንገዶች አሉት በዚህ ዓለም ብዙ የሚወደዱ ነገሮች አሉ ለምሳሌ ፣ አባትና እናት
ይወደዳሉ ፣ በሥጋ ወልደው በወተት በፍትፍት አሳድገው ለቁም ነገር ያበቃሉና ሚስትም ትወደዳለች በኑሮ
ትረዳለችና ልጆችም ይወደዳሉ ሲጠሯቸው አቤት ሲልኩአቸው ወዴት በማለት ያገለግላሉና ከእነዚህ ከተጠቀ
ሱት ሌላ እህት ፣ ወንድም ፣ ዘመድ ፣ አጐት ፣ መልካም ጐረቤትና የመሳሰሉት ይወደዳሉ እግዚአብሔር አምላካ
ችን በደብረ ሲና ለሙሴ ሕዝቡን እንዲያስተዳድርባቸው ከሰጠው ትእዛዛት አንደኛውና የመደምደሚያው
ወንድምህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ የሚለው ቃል ነው ።

የቀሩት ትእዛዝት ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክና ወንድምህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ በሚ
ሉት ሁለት ትእዛዛት እንደሚጠቃለሉ ተጽፎአል ።

እግዚአብሔርን መውደድ ማለት ጣዖት አበጅቶ ምስል ሠርቶ ለዚያ አለመስገድ አለመውደቅና አለመ
ነሣት ለጣዖት ደም አለማፍሰስ ስብ አለማጤስ ቆሎ እየቆሉ አለመበተን ቂጣ እየጋገሩ እየቆረሱ አለመጣል
ሰማይንና መሬትን ከፈጠረ አምላክ በስተቀር ሌላ አዳኝ አለመኖሩን ተረድቶ በእግዚአብሔር ብቻ አምኖ
መኖር ነው ወንድምን መውደድ ደግሞ ቤቱን ንብረቱን አለመመኘት በጉቦ ተደልሎ በሐሰት በወንድም ላይ
አለመፍረድና አለመመስከር እኔን እንደሚርበኝ እኔን እንደሚጠማኝ እኔን እንደሚያርዘኝ ሌላውንም ይርበዋል
ይጠማዋል ያርዘዋል ብሎ ማሰብ ነው "ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድ
ርጉላቸው ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና" ተብሎ እንደተጻፈው ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ ሊደረግበት የማይወ
ደውን በሌላው ላይ እንዲደረግበት አለመመኘት ነው ፤

ሐዋርያው ጳውሎስ የፍቅርን ከፍተኛነት ሲገልጽ እምነት ተስፋ ፍቅር ለዘለዓለም ጸንተው ይኖራሉ
ካሉ በኋላ ከእነዚህም የምትበልጠው ፍቅር ናትና ፍቅርን ተከተሏት ብሏል ።

ወንጌላዊው ዮሐንስ በመልእክቱ ስለ ፍቅር ሲናገር "ዓለሙን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ በዓ
ለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለገንዘብም መመካት ከዓለም ነው እንጂ ከአባት
ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም ፣ ዓለሙም ምኞቱም ያልፋል የእግዚአብ
ሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል" ብሏል ሐዋርያው ዓለሙንና በውስጡ ያለውን አትውደዱ
ማለቱ ዓለሙን ለማስጠላት አይደለም ሕጉን ጠብቆ ሥርዓቱን አክብሮ ቢኖሩበት የሚያስደስት ሲሆን ከሕጉ
ከወጡ ደግሞ አስደሳች መሆኑ ቀርቶ የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ ይሆናል ።

በዚህ ቃል መነሻነት መተርጉማን መጻሕፍት የሚከተለውን ምሳሌ ይናገራሉ በአንድ ላይ በጓደኝነት
የሚኖሩ ሁለት ሰዎች ነበሩ ፍቅራቸው እጅግ በጣም የጠነከረ ስለነበር ጧት ለሥራ ተለያይተው ማታ እስከሚ
ገናኙ ድረስ ይነፋፈቁ ነበር አንዱ ቀደም ብሎ ከቤቱ የደረሰ እንደሆነ የቀረው እስከሚመጣ ከደጅ ወጥቶ ይጠ
ብቀዋል በተገናኙም ጊዜ ብዙ ቀን ተለያይተው እንደሰነበቱ ይሳሳማሉ ፤

በዚህ ሁኔታ ብዙ ዘመን አብረው ኑሮዋል ከዕለታት አንድ ቀን አብረው መንገድ ሲሄዱ ብዙ ወርቅ
አገኙ ሁለቱም እጅግ በጣም ተደስቱ ነገር ግን ወርቁን ካገኙ ጀምሮ በእያንዳንዳቸው መንፈስ ሰይጣን ስላደረ
ባቸው በክፉ ነገር እርስ በእርሳቸው ይፈላለጉ ጀመር አንደኛው ይህ ወንድሜ ሞቶልኝ ይህንን ወርቅ ብቻዬን
ወስጄ ተጠቅሜበት እያለ ወንድሙ የሚጠፋበትን መንገድ ሲፈልግ ሌላውም በበኩሉ ይህንን የመሰለ አሳብ
በልቡ ስለተፀነሰ ያወጣና ያወርድ ነበር ።

በመካከል ላይ አንደኛውን ኮሶ፡ስለታየው ወንድሜን መድኃኒት በጥብጠህ አጠጣኝ እለዋለሁ በጥብ
ጦም ሲያቀርብልኝ አንሥተህ ስጠኝ እለዋለሁ አንሥቶ ለመስጠት ጐንበስ ሲል በሰይፍ አንገቱን ቆርጬ
ገድዬ የተዘጋጀውን መድኃኒት በመጠጣት ከኮሶዬ ሽሬ ወርቁንም ለብቻዬ እጠቀምበታለሁ ብሎ አስቦ ወንድ
ሙን እባክህ የኮሶ መድኃኒት አጠጣኝ አለው ።

ያም በበኩሉ ጓደኛውን ገድሎ ወርቁን ለብቻው ለመውሰድ አስቦ ስለነበር እሺ ብሎ ከመድኃኒቱ ጋር
የሚገድል መርዝ አዘጋጅና ወንድሙን ጠርቶ አዘጋጅቼልሃለሁና መጥተህ ጠጣ አለው መጥቶም ያንን የተበጠ
በጠ መድኃኒት አንሥተህ ስጠኝ አለው አንሥቶ ለመስጠት ጐንበስ ሲል በሰይፍ አንገቱን ቆርጦ ገደለው እንግ
ዲህ እርሱን ከገደልኩ መድኃኒቱን ጠጥቼ ከኮሶዬ ሽሬ ወርቁንም ብቻዬን እወስዳለሁ አለና ያንን መድኃኒት
አንሥቶ ቢጠጣው መርዝ ተደባልቆበታልና ወዲያውኑ ገደለው ሁለቱም ሲሳሱለትና ሲንገበገቡለት የነበረው
ወርቅ ወሳጅ አጥቶ እንዲሁ ቀረ ይባላል ።

በዓለም የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ለሰው መገልገያና አገልጋይ እንዲሆን ነው እንጂ ከሰው በላይ በመ
ሆን ለሕይወቱ ማጥፊያ እንዲሆን አይደለም ሰው ከእናቱ ማኅፀን ሲወጣ ገንዘብ ይዞ አይወለድም መሬት ነህና
ወደ መሬት ተመለስ የሚለው ጥሪ በደረሰውም ጊዜ ወደ መሬት የሚገባው ርቃን ሥጋውን ነው ታዲያ በብዙ
ድካም ወጥቶ ወርዶ ነዶ በርዶ ለሚገኘው ገንዘብ ተገዥ በመሆንና ከራሱም አብልጦ በመውደድ በእርሱ ፍቅር
ሕይወቱ ሥጋውን ማሳለፍ አይገባውም ።

በገንዘብ ፍቅር ሕይወተ ሥጋቸውን ያሳለፉት ከላይ የተጠቀሱት ብቻ አይደሉም ይሁዳና የመ
ሳሰሉም ይገኛሉ ይሁዳ ከገንዘብ ፍቅር የተነሣ ፈጣሪውን ለሰላሳ ብር ሸጦ በገንዘቡ ሳይጠቀምበት
ብሩን በአቴናው ላይ በትኖ ታንቆ ሙቷል ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ የሚል የአባቶች አነጋገር አለ ቢሆ
ንም በተገቢው መንገድ ሲያውሉት ነው እንጂ ከራስ አብልጦ እንዲወደድ አይደለም የተፈጥሮ ወገኖቻችን
እንደ ራሳችን አድርገን እንድንወድ ታዝዘናል እንጂ ገንዘብን እንደራሳችሁ ውደዱ የሚል ቃል በቅዱሳት መጻ
ሕፍት ተጽፎ አናገኝም ።

ወንጌላዊው ዮሐንስ በመልእክቱ "ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም እግዚአብሔር ፍቅር
ነውና ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም ፍርሃት መቅሠፍት አለውና የሚፈ
ራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን ማንም እግዚአብሔርን እወዳ
ለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሠተኛ ነው የሚያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን እን
ዴት ሊወድ ይችላል ? እግዚአብሔርን የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን
ሲል ተናግሯል ፩ኛ ዮሐ ፬.፰።

ወንድምህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ እንደተባለው ፍቅራችን በተፈጥሮ ወንድማችን ላይ የተመሠ
ረተ መሆን አለበት እንጂ በገንዘብ ፍቅር ላይ ያተኮረ መሆን የለበትም ፍቅራችን እውነተኛ ፍቅር ከሆነ እርስ
በእርሳችን እንፈራራም አንዱ ሲሳሳት ሌላው ስሕተቱን ይነግረዋል ስሕተተኛውም ከስሕተቱ ለመመለስ ይች
ላል ፍቅራችን ግብዝነትን የተሞላ ከሆነ ግን በመካከላችን የሚፈጸመውን ስሕተት አውጥተን ለመናገርና ለማ
ስወገድ ስለማንችል በስሕተት ላይ ስሕተትን እየጨመርን እንሔዳለን ።

ይህ እንዳይሆን እግዚአብሔርን የምንወድ በእርሱ ስም አምነን ጸንተን የምንኖር ሁሉ ፍቅራችን የሚገ
ለጸው በተፈጥሮ ወገኖቻችን ላይ በምናሳየው መልካም ተግባር ስለሆነ በፍቅራችን ፍርሃት ሊኖርበት አይ
ገባም ።


www.ethiopianorthodox.org

# "እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው"

ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋራ ነውና ይህ ከላይ ርእስ እንዲሆን የተመረጠው ቃል፡ ወልደ እግዚአብሔር ሰው የሚሆንበት ጊዜ ሲደርስ መልአኩን ቅ/ገብርኤልን ሒድና ለድንግል ማርያም የምሥራች እንዲህ ብለህ ንገራት ብሎ ላከው በዚህ ጊዜ መላእኩ ቅ/ገብርኤል ይህንን የደስታ መልእክት ይዞ መጥቶ "ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋራ ነውና ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ" ሲል የምሥራች የደስታ ቃል ስላቀረበላትና ቡርክትነቷንም ስለመሰከረላት ነው። ሉቃ ም. ፩ቁ. ፳፮-፳፰።

ተመልከት መልአኩ ቅ/ገብርኤል ይህንን የምሥራች ቃል ለእመቤታችን የነገራት በታችኛው ገሊላ አውራጃ በዘመነ ብሉይ በተለይ ናዝሬት ተብላ በምትጠራው ከተማ ነው ይሁን እንጂ ይህች ከተማ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ገሊላ ተብላ በጠቅላላ በአውራጃው ስም ከመጠራት በስተቀር ሌላ የተለየ ስም አልነበራትም ይህች ከተማ በተለይ የምትገኝበት ቦታ ከገሊላ ባሕር ወይም ከጥብርያዶስ በስተምዕራብ ፳፭ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ባለው በነገደ ዛብሎን ዕጣ ውስጥ ከቀርሜሎስ ተራራ ስር ከምሥራቅ በኩል የተመሠረተች ከተማ ከመሆኗም በላይ ደብረ ታቦርናይንና ቀርሜሎስ የሚያማክሏት ከተማ ናት "በዘመነ ብሉይ የሚኖሩበት ሰዎች እጅግ የተናቁና የተዋረዱ ስለነበሩ ስሟን እንደ ብዕዓት ልጆች በጎብረት ከሚኖሩባት (ሕዝብ) ሰዎች ወርሳለች። ይኸውም ማኅደር በኃዳሪ ኃዳሪ በማኅደር መጠራት ክጥንት ሲያያዝ የመጣ ልማድ ነውና ኋላም የተነገረው ትንቢት የተ ቈጠረው ሱባዔ ሲደርስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተፀነሰባት ያደገባትና የኖረባት ከተማ ናት (ሉቃ ፩፣ ፳፮-፳፯)።

ይኸውም አስቀድሞ አምስት ቀን ተኩል ማለት አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ሲል ለአዳም በሰጠው የተስፋ ቃል ወይም ከርሞ እንደ ዛሬ ወደ አንተ እመለሳለሁ ብሎ ርእስ አበው ለመ ዓለም ከአብ ያለ እናት እንደ ተወለደ ድኅረ ዓለም በተለየ አካሉ በቃሉነቱ ሰው ሆኖ ማለት ሥጋንና ነፍስን ተዋህዶ ያለ አባት ከድንግል ተፀንሶ ይህችውም ከዓበይት ነቢያት ወገን በተለ



ምስለ ምቁር ወልዳ

ሆነው ለአብርሃም መጀመሪያ በሰጠው በሁለተኛው ግን እኔ ራሴ ሰው ሆኜ ሥጋ ለብሼ ዓለምን እጐበኛለሁ ብሎ ለዕዝራ የተናገረ ወልድ ዋህድም ቅድ ይ ኢሳይያስና ሕዝቅኤል የተናገሩላት ወይም የመሰከሩላት ድንግል ማርያም ናት። (ሕዝ. ፵፬፣፩-፪)

ስለዚህ ከላይ እንደተናገርነው ልዑል እግዚአብሔር በሦስትነቱ ለርእሰ አበው ለአብርሃም በተገለጠ ጊዜ እግዚአብሔር ወልድ የዛሬ ዓመት እኔ ወደ አንተ እመለሳለሁ ብሎ በቃልነቱ ሲናገር ሥጋ በአብርሃምነት ቆሞ ተስፋውን ይቀበል እንደነበር ግልጽ ነው (ዘፍ ፲፰. ቁ. ፱-፲) እንግዲህ ነቢዩ ኢሳይያስ ዓማኑኤል ዳንኤል ክርስቶስ መልአኩ ቅ/ገብርኤል ኢየሱስ ብለው የጠሩት ኖሎት መላእክት በቤተ ልሔም በአንድነት "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ" ብለው ያመሰገኑት ስብእ ስገል የሰገዱለት ወርቅ ዕጣን ከርቤ ይዘው መጥተው የገበረለት ድንግል ማርያም እናቱም አውራ ማተን ያሰረችው በጨርቅ የጠቀለለችው ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ በመሆኑ ነው ማለት አምላክ ሰው ሰው አምላክ በመሆኑ ነው ከላይ ነቢዩ ኢሳይያስ ዐማኑኤል ያለው ቃል ጥሬው ዕብራይስጥ ነው ይኸውም ከሚጠራባቸው ስሞቹ አንዱ ነው በዕብራይስጡ ቋንቋ አማኑ" ማለት በግዕዝ ቋንቋ ምስሌነ ማለት ሲሆን በአማርኛችን ደግሞ "ከእኛ ጋር ማለት ነው" በዕብራይስጥ "ኤል" ማለት በግዕዝ እግዚአብሔር ወይም አምላክ ማለት ሲሆን በአማርኛችንም አይለወጥም አንድ ነው በተገናኝ በዕብራይስጡ ቋንቋ "አማኑኤል" ሲል በግዕዙ እግዚአብሔር ምስሌነ" ማለት ሲሆን በአማርኛችን ግን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው የኢትዮጵያ ሊቃውንት" አምላክ ወሰብእ" ብለው ይተረጉሙታል አስተውል ፪ኛ ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ቤዛ መቤዠው ማለት ነው ይሁን እንጂ ዕብራይ ሰጡ "የሹዕ" ዓረብኛውም "የሱዓ" ወይም የሱዕ ሲል ግዕዝም ሆነ አማርኛችን "ኢየሱስ" ይላል ይህንንም የኢትዮጵያ ሊቃውንት በመተንተን ሲያስረዱ "ኢ"ን ያገቡት አይሁዶች ናቸው ይኸውም "አኮ መድኃኒት" ለማለት እንዲመቻቸው ጨምረውታል ሲሉ ያትታሉ ይሁን እንጂ ሐተታውን ለመቀበል የሚያስችለው "ኢ" የሚባለው ፊደል በዕብራይስጡ ቋንቋ ለማስረጃነት ተጽፎ ቢገኝ ነበር ነገር ግን ሐተታው የፊደሉን የት መጣ ሳይሆን የአይሁዶችን ግብራቸውን" ማለት ፀልዑ ዘእምአፍቀሩ መድኃኒተሙ ሰቀሉ" ያለውን ቃል ያሳስባል ፫ኛ ክርስቶስ መሲሕ ማለት ነው ይኸውም ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባህርይ መጀመሪያ መልአኩ ቅ/ገብርኤል ይህን የምሥራች ይዞ መጥቶ እመቤታችንን ያነጋገራት በታችኛው ገሊላ አውራጃ የምትገኝ ናዝሬት የምትባል ከተማ መሆኗን በተቻለ መጠን የጻፍኩ መሆኔን እየገለጽኩ ከዚሁ በማያያዝ መልአኩ ቅ/ገብርኤል "ድንግል ማርያም ሆይ አይዞሽ በዚህ በምነግርሽ ቃል አትጠራጠሪ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋን አግኝተሻልና" እያለ ከአጽናናት በኋላ "እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ" ብሎ የምሥራቹን ነገራት (ሉቃ ፩፡፴፪-፴፫) ከዚህ አያይዞ ወዲያው የልጅዋን ታላቅነት የልጅዋን አምላክነት ሲያስረዳት "እርሱም ታላቅ ነው የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል በያዕቆብ ወገን ለዘለዓለሙ ይነግሣል ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም" ብሎ ከነገራት በኋላ እመቤታችንም ራሷን ለእግዚአብሔር ብፅዓት አድርጋ እስከ መጨረሻ ሰጥታ ነበርና የመልአኩ አነጋገር ቢረቅባት ወደፊት የማታየርገው መሆኑን ለመግለጽ" ምድር ያለ ዘር እህል እንደ ማታስገኝ ሴትም ያለ ወንድ ልጅ እንደ ማታስገኝ ሁሉ ታውቃለችና ይህ ነገር እንደምን ሊሆን ይቻላል ማለት ወንድ ሳላውቅ ፀንሶ መውለድ እንደምን ይቻላል ስትል በጥያቄ መልክ ነገሩን ባቀረበችለት ጊዜ መልአኩ ቅ/ገብርኤልም እንዲህ ሲል መለሰላት የአንቺ ፅንስ ከሰው ልማድ ልዩ ነው ለማለት" መንፈስ ቅዱስ ወደ አንቺ ይመጣል የልዑል ኃይልም ይጋርድሻል ይጸልልሻል ብሎ ከሴቶች ልማድ ልዩ መሆኗን አስረድቷታል ይኸውም ይጋርድሻል ይጸልልሻል የሚለው ኃይለ ቃል የእግዚአብሔር ሥልጣን ከሴቶች ልማድ ከወንድ ከመገናኘት ዘር ከመቀበል ከድንልና ከመለየት ከዚህ ዓለም ነገር ሁሉ ይከለክልሻል ይጠብቅሻል ሲል ነው አስተውል ።

መልአኩ ቅ/ገብርኤል ነገሩን ከዚሁ በማያያዝ በምሳሌ ለማሳመን... "እነሆ ኤልሳቤጥ እንኳ ዘመድሽ በእርጅናዋ ወራት ፀንሳለች" ካላት በኋላ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና" የእግዚአብሔርን ኃይል የእግዚአብሔርን ሥልጣን የነገሩ መዝጊያ አድርጎ ቢነግራት እርሷም ሌላ ጥያቄ ማቅረብ ተገቢ አለመሆኑን ተረድታ በአጭሩ የሰጠችው መልስ እነሆ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ እንዳልከኝ ይሁንልኝ" ባለችው ጊዜ ቃሏን ምክንያት አድርጐ በግብረ መንፈስ ቅዱስ መጋቢት ፳፱ ቀን በ፫ ሰዓት ጌታ ሰው ሆነ ።

መልአከ ኃይል ወ ያሬድ መኩሪያ

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ሥጋ መስለው እንደሚቀርቡ የታመነ ነው ። ከዚህ በቀር ልቡሳነ ሥጋ ናቸው ከብት ያረባሉ እንደ ሰው ይታመማሉ ይሞታሉ የሚለው አስተሳሰብ የሚታመንበት አይደለም ።

አራተኛ ያላመነና ያልተጠመቀ ሰው በሞተ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐት ሊደረግለትና በአውደ ቤተ ክርስቲያን ሊቀበር ይገባዋልን ስላልከው ያላመነና ያልተጠመቀ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀርብ ሕገ ቤተ ክርስቲያን አይፈቀድም ። ፍትሐ ነገሥት ፍ. መ አንቀጽ ፲፱ ተመልከት ።





www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ስትቋቋምና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ሲመሠርታት የተራራቁትን ሕዝብ በማቀረብና የተበተኑትንም ምእመናን በመሰብሰብ ነበር በዚያን ጊዜ የነበሩት የመጀመሪያዎቹ አማኞች ክርስቲያኖች ገንዘባቸውም ሆነ ንብረታቸው ሁሉ አንድ ላይ ነበር እንጂ ልዩነት አልነበረውም በመካከላቸውም ይህ የእኔ ነው ይህ ያንተ ነው የሚል ትራፊ ፈጽሞ የሚያወሳ እንዳልነበር ሲያረጋግጥ ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ ያላቸውንም አንድነት አደረጉ ይላል የሐዋ ሥራ ፪፥፵፬=

ይህንንም መሠረት በማድረግ በአርሁት ምንኩስና የተጠመዱ ቅዱሳን ገዳማትን የመሠረቱ የአንድነትንም ገዳም ያቋቋሙ ብዙዎች ናቸው ከብዙዎቹም አንዱ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ስለሆኑ ባሁኑ ልማት በቤተ ክርስቲያን ጽሑፋችን በአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ገዳም በደብረ በንኩል ምን ዓይነት ልማት እንደሚካሄድ እንገልጻለን ።

በቅድሚያ ግን የአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ወላጆች እነማን እንደሆኑ እናስተዋውቃችሁ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በኤርትራ ክፍለ ሀገር ስንዓፌ ወረዳ ልዩ ስሙ ቢሐት በተባለው ቀበሌ ከአባታቸው ከቴስ ተስፋ ሰንበት ከእናታቸውም ከሕሪተ ማርያም ተወለዱ በዚያው በተወለዱበትም አካባቢ ተምረው ና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አጠናቀው ሲያበቁ ጐናጕና በተባለው ገዳም በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እጅ መነኮሱ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ ከጐናጕና ወደ አክሱም አውራጃ እንዲሄዱና በዚያ የአንድነትን ገዳም አቋቁመው እንዲኖሩ አዘዛቸው አቡነ መድኃኒነ እግዚእም ትእዛዙን ተቀብለው በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል መሪነት ደብረ በንኩል ገብተው በጾምና በጸሎት ተወስነው ሲኖሩ ደግነታቸውና ቅድስናቸው በሁሉም ስለታወቀ ብዙ መነኮሳት ተሰበሰቡ በዚህ ጊዜ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ የአንድነት ገዳም አቋቁመው በዚሁ ቦታ ታቦተ ማርያምን ተክለው ኖሩ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በነበሩበት ዘመን ፻፺፱ መነኮሳት እንደ ነበሩ ገድላቸው ይናገራል ።

ደብረ በንኩል ብዙ ቅዱሳን የተወለዱበት ታላቅ ገዳም ነው ለምሳሌ በደብረ በንኩል ከተወለዱት ብዙዎች ቅዱሳን መካከል በጥቂቱ መግለጽ ቢያስፈልግ እነ አቡነ ሳሙኤል ዘቆየጻ እነ አቡነ ዓምደ ሥላሴ የመሳሰሉት ቅዱሳን ሁሉ ከዚሁ በደብረ በንኩል ገዳም ከአቡነ መድኃኒነ እግዚእ በመንፈስ ቅዱስ የተወለዱ ናቸው ። ታድያ ባሁኑ ጊዜ የደብረ በንኩል ገዳም እንዴት እንደሚተዳደር እንዲገልጹልን ከዚያው ገዳም በምናኔ የሚኖሩትን መምህር ገብረ ኢየሱስ ኪዳነ ማርያምን ጠይቀናቸው ሲመልሱ ገዳሙ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ከቆረቆረበት ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ ባንድነት ነው የሚኖረው አንድነትም ሲባል መነኮሳቱና ያልመነኮሱት ሁሉ ከገዳሙ ከገቡ ትልቅ ትንሽ ሳይባል ሁሉም አንድ ላይ ይሠራሉ በአንድነትም ቤተ ክርስቲያንን ያገለግላሉ ።

ትንግሥ=

በገዳሙ ልማት ነክ የሆኑ ነገሮች እንዳሉ ቢገልጹልን?

መልስ፡ ልማት በየዓይነቱ እናለማለን ከምናለማቸው ልማቶች

፩ኛ ቡና
፪ኛ ሙዝ
፫ኛ ብርቱካን
፬ኛ ሎሚ
፭ኛ ትርንጎ
፮ኛ ጌሾ የመሳሰሉት ሲሆን ሌሎችም ኅምን ቲማቲም የመሳሰሉትም በብዛት እናለማለን ።

ትንግሥ፡

ከእነዚህ አትክልት የሚገኘው ፍሬ ለምን ተግባር ይውላል?

መልስ፡ ሙዙንና ብርቱካኑን ሸጠን ልብስ ለማንኛውም ለገዳሙ እናውላለን የቀረውን ደግሞ ማኅበሩ በሙቁነን ይጠቀምበታል ።

ትንግሥ፡ አትክልቱን የሚንከባከበው ማን ነው? የተወሰኑ ሰዎች አሉ ወይስ ሰው ተቀጥሮ ነው ፧

መልስ፡

እኛ ራሳችን ተራ በተራ ውኃ እናጠጣለን እንኮተኩተዋለን ። በዚህ መልክ ነው የምንከባከበውና የምንጠብቀው ምግባችሁስ እንዴት ነው የምታገኙ?

ትንግሥ ፡-

መልስ፡

ምግባችንን የምናገኘው በእርሻ ነው ከገዳሙ የገባ ሁሉ ጉልበት ያለው ያርሳል ይቆፍራል እንጨት ይቆርጣል ውኃንም ይቀዳል እንደዚሁ ደግሞ አረጋውያን ጉልበት የሚያንሳቸው ሁሉ በገዳሙ ሁነው ይጸልያሉ እንጀራንም ይጋግራሉ በጠቅላላ የሚቻላቸውን ሥራ ይሠራሉ ስለዚህ ጉልበት ያለው በእርሻ ሲያገለግል ጉልበት የሌለው ደግሞ በቤት በገዳም ውስጥ ይሠራል ማለት ነው ።

ትንግሥ፡

እርሻንስ የሚያርሱ እንዴት ያሉ ናቸው?

መልስ፡

ገዳሙ ፡ ከላይ እንደ ገለጽኩት የአንድነት ገዳም እንደመሆኑ መጠን ሲያርሱ የሰነበቱ መነኮሳት ወደ ቅዳሴ ይመለሳሉ ሲቀድሱ የሰነበቱት ደግሞ ወደ እርሻ ይሄዳሉ ስለዚህ የሚቀድሱም የሚያርሱም ራሳቸው መነኮሳቱ ናቸው ።

ትንግሥ፡

በገዳሙ መምህራን አሉ ወይ?

መልስ፡

በገዳሙ ብዙ መምህራን ነበሩ ። ባሁኑ ጊዜ ግን አንድ የአቋቋም አንድ የቅዳሴ አንድ የንባብ በጠቅላላ ፫ መምህራን ሲኖሩ ቀደም ሲል ግን የመጽሐፍ መምህራንም ነበሩ ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ በዚህ የመምህራን እጥረት



# አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

የጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አባታቸው ስምዖን ሲሆን እናታቸው አቅሌስያ ትባላለች በሕግ ተጋብተው

---

አለብን ።

ትንግሥ፡

ከላይ የተጠቀሱት መምህራንስ ደመወዝ ከምን ያገኛሉ?

መልስ፡

ገዳሙ ምንም ሁሉን ቢያውቅ የአንድነት ስለሆነ ደመወዝ የሚከፈለው መምህር የለም በገዳሙ ውስጥ ሀብታምና ድኃ ትልቅ ተብሎ የሚለይ የለም ሁሉም ትክክል ነው ።

ትንግሥ፡

በገዳሙ ችግር አለ ብለው የሚገምቱት ነገር እንዳለ ቢያስረዱን?

መልስ፡

በገዳሙ ያለው ትልቅ ችግር ውኃ ነው በገዳሙ ውስጥ ውኃ የለውም ከሩቅ ቦታ በአህያና በበቅሎ በሸራ ነው የሚመጣው እንጂ በቅርባችን ውኃ አናገኝም ።

ስለ ውኃ ችግር ያቀዳችሁት ዕቅድ ይኖራል ?

መልስ፡

ስለ ውኃው ችግር ጉድጓድ ተቆፍሮ የውኃ ማጠራቀሚያ ኩሬ እንድንሠራ ሕዝቡን ከማስተባበራችንም በላይ ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያም እየመለከትን ነን ።

ገዳሙ የውኃ ችግር እንዳለበት ያለ ውኃም መኖር እንደማይቻል የታወቀ ነው ። ስለዚህ አበው መነኮሳት የሚጸልዩበትና ልዩ ልዩ ትኩረት የሚፈጸሙበት ብዙ ድኩማንም የሚረዱበት ስለሆነ ያለው በገንዘቡ የሌለው ደግሞ በሐሳቡ ቢፈጽም መልካም ነው ተስፋም አይታጣበትምና የሚመለከተው ሁሉ ቢያስብበት መልካም ነው ።

ከልማቱም አንዱ ውኃውን ቆፍሮ ማውጣት ነውና

ከንፈ ርግብ ማርቆስ

አሥራቱን በኩራቱን እየከፈሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቀው ይኖሩ ነበር ፤ ነገር ግን ልጅ አልነበራቸውም ልጅ እንዲሰጣቸው ወደ እግዚአብሔር በመለመን ያለልጅ ፴ ዓመታት ኑረዋል ።

ሀገራቸው በግብጽ በስተደቡብ ንሒ



ሳ የሚባል ነበር ይህንን አንድ ደራሲ ሲገልጽ ስምዖን ወአቅሌስያ ዘነበሩ በንሒሳ በኃጢአ ውሉድ በከዩ መጠነ ዓመ

ታት ሰላሳ ብዒል ወደአማርኛ ሲተረጐም በንሒሳ ይኖሩ የነበሩ ስምኦንና አቅሌስያ ልጅ ባለማግኘታቸው ሰላሳ ዘመን ሙሉ አለቀሱ ማለት ነው ።

ስምኦንና አቅሌስያ መጋቢት ፳፱ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔደው የሥላሴ ሥዕል ወደአለበት ቀረብ ብለው "የፈጣሪውን ትእዛዝና ሕግ የሚጠብቅ ልጅ ስጠን" ብለው ተማፅነው እንደተመለሱ ማታውኑ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተጸነሱ ።

ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከ



www.ethiopianorthodox.org

ተጸነሡ ጀምሮ የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነት ከአቅሌስያ አልተለየም የመውለጃዋ ቀን ሲቃረብ ቅዱስ ገብርኤል በግልጽ ወደ እርሷ መጥቶ ከአንች የሚወለደው ልጅ እጅግ በጣም ትልቅ ነው ብሎ ነግሯት ተሠውሯል ።

ታኅሣሥ ፳፱ ቀን በመንፈቀ ሌሊት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሲወለዱ የተወለዱበት ቤት ግቢውም ሆነ ውጭ ብርሃን ሆነ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም የእናታቸውን ጡት ሳይቀምሱ አፈፍ ብለው ተነሥተው ከጨለማ ወደ ብርሃን ለአወጣኸኝ ፈጣሪ ክብርና ምስጋና ይገባሃል ብለው ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ሦስት ጊዜያት ሰግደዋል ፤ ወላጆቻቸው ስምዖንና አቅሌስያም በልጃቸው በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የተደረገውን ተአምር አይተው አደነቁ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ በአካባቢው የሚገኙትም ሕዝብ ሁሉ ይህንን ተአምር ስላዩ እየመጡ እግዚአብሔርን አመሰገኑ በሦስተኛውም ቀን መልአኩ ቅ/ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ መጥቶ ስሙን ገብረ መንፈስ ቅዱስ በሉት ብሎ ነግሯቸው አርጓል ።

እንዲሁም ሦስት ዓመት ሲሆናቸው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከአምላክ ታዝዞ መጣና እየመራ ወስዶ በአካባቢው ለሚገኙት የገዳም አስተዳዳሪ ለነበሩት አባ ዘመደ ብርሃን አስተምሩት ብሎ ሰጣቸው ።

አባ ዘመደ ብርሃንም ይህንን ሕፃን ተቀብዬ ምን እመግበዋለሁ ? ምንስ አለብሰዋለሁ ? ብለው ሲጨነቁ ቅዱስ ገብርኤል ስለምግብና ልብሱ አትጨነቅ ሕፃኑ ምድራዊ ምግብ ምድራዊ ልብስ የሚያስፈልገው አይደለም እግዚአብሔር ያዘለታል ብሎ ስላስረዳቸው ተቀብለው ያስተምሯቸው ጀመር ትምህርታቸውን ሲጨርሱ አቡነ አብርሃም ከሚባሉ ጳጳስ ወስደው ፩ህነት እንዲቀበሉ አድርገዋቸው ተቀብለዋል ። ቀጥሎም እንደነ አባ እንጦንስ ምንኩስናን ተቀብለው ለብዙ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ደካሞችን ሲረዱ ወንጌልን ሲያስተምሩ ከኖሩ በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን ጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ ከእንግዲህ ወዲህ የዓለም አባት አደርግሃለሁና ከሰው ተለይተህ በበረሃ ኑሮ አብረውህ የሚኖሩ ጓደኞች ፳ ነብሮች ፤ ፳ አንበሶች ሰጥቸሃለሁና አብረህ ኑር ቢላቸው እሺ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ነገር ግን ምን እመግባቸዋለሁ ቢሉት ስለአንተ ክብር እንደ አንተው የማይበሉ የማይጠጡ አደርግልሃለሁ የቆምክበትን መሬት ይላሱ መዓዛህንም ያሸቱ፥ ምግብም ይሆናቸዋል ብሎ አቸዋል ። በዚህም መሠረት እነዚህ የተጠቀሱት ግሩማን አራዊት ከጻድቁ ሳይለዩ ብዙ ዘመን አብረው መኖራቸውን ገድላቸው ይናገራል በምድረ ግብጽ ፻፶ ዓመታት ከኖሩ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል በመጀመሪያ አክሱም ጽዮን ደርሰው ለጥቂት ቀናት ሲጸልዩ ከሰነበቱ በኋላ ላስታ ሮሃ ቤተ መንግሥት መጥተው በዚያን ጊዜ ንጉሥ ከነበረው ላሊበላ ጋር ተገናኝተዋል ።

ላሊበላም የጻድቁን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ላህይና ሁኔታ ተመልክቶ በጣም ተደሰተና የተለየ የክብር ቦታ ሰጣቸው አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ጥቂት ቀን እያስተማሩ በሮሃ ቤተ መንግሥት ሰነበቱ ቅዱስ ላሊበላም አባቴ ቦታ ልስጠዎትና በዚሁ እየጸለዩ እየባረኩ ወንጌልንም እያስተማሩ ይቀመጡ አላቸው ።

ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እኔ እንዳስተምር እንድጸልይ የታዘዝኩት በደብረ ታቦር አምሳል በሆነች በዝቋላ ተራራ ስለሆነ ወደዚያ እሄዳለሁ የአንተ ግን ከተማህ የተባረከ ነው አንተም የተባረክህ ነህ እኔ ግን ወደዝቋላ መሄዴ ነው ብለው ሲነሡ አባቴ ሆይ አብሬ ሂጄ አድርሽዎ እንድመለስ ይፍቀዱልኝ አላቸውና ፈቀዱለት ላሊበላም ሠራዊቱን አስከትሎ ተከትሏቸው ወደ ዝቋላ መጣ ደብረ ዘይት አጠገብ ቆፍቱ ላሊበላ ከሚባለው ቦታ ደርሰው ባደሩ ጊዜ በዚያ ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያን እንደሚሠራ ተገልጾላቸው ትንቢት ተናግረዋል ።

ዝቋላ ተራራም እንደደረሱ ከዚያ በፊት ታቦተ ማርያም ተተክላ ቤተ ክርስቲያን ነበርና መካከሉ ገነት ዳሩ እሳት ይሁን የበረረ ወፍ ፤ የሰገረ ቆቅ የበደለ ወንጀለኛ አይታደንበት ብሎ ገድሞላቸው በሚመለስበት ጊዜ በመንገድህ ላይ አዳዲ ከምትባል ቦታ ላይ በላስታ እንደሚገኙት አብያተ ርስቲያናት ፈልፍለህ ሠርተህ ታቦተ ማርያም አስገብተህ በቶሎ ወደ ቤተ መንግሥትህ ተመለስ ጊዜ ዕረፍትህ ተቃርቧል ብለው መከረው ሰደዱት እንደነገሩት አዳዲ ላይ ቋጥኙን በመፈልፈል ቤተ ክርስቲያን አሠርቶ ታቦተ ማርያምን አስገብቶ ወደ ቤተ መንግሥቱ እንደተመለሰ ብዙ ዓመት ሳይቆይ አርፏል ።

አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም በዝቋላና በምድረ ከብድ የአንድነት ገዳም ብመመሥረት ብዙ መነኮሳትን ሰብስበው ብዙ ገድልና ትሩፋት ሠርተዋል ወንጌልንም በኢትዮጵያ አህጉረ ስብከት እየዞሩ አስተምረዋል ።

ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በሀገራችን በኢትዮጵያ ፪፻፷፪ በግብጽ ፻፶ በድምሩ ፭፻፷፪ ዓመት በስብከተ ወንጌል በጾም በጸሎት በስግደት ኑረው መጋቢት ፭ ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

## ከቋጥኝ ድንጋይ...

ከገጽ ፳፱ የዞረ

ጥንታዊትና ቅርሳቅርስ ጠብቃ የምትኖር ታላቅ ሀገ ር ናት በዚህችም ታላቅ ቤተ መቅደስ እመቤታችንን ከልጅዋ ከኢየሱስ ጋር በእንግድነት ያረፈችበት ስለሆነ ልናከብራትና ልንማፀንባት ይገባል የዚህችም ቤተ ክርስቲያን የመታሰቢያ በዓል ግንቦት ፩ ቀን እና ሰኔ ፳፩ ቀን በየዓመቱ በከፍተኛ ሥነ ሥርዓት ይከበራል ።

የዜናው አቅራቢ አባ ገብረ መስቀል
ተስፋዬ ዘገነተ ማርያም



# ዜና ሊቃውንት

## ፴ ዓመታት ሙሉ የሐዲስ ጉባኤ ዘርግተው የሚያስተምሩት መምህር ብርሃኑ ወልደ ሥላሴ

መምህር ብርሃኑ በሸዋ ክፍለ ሀገር እንሳሮ አውራጃ ከመምሬ ወ/ሥላሴ አብዩ እና ከወ/ሮ እህትአየሁ ባሴ ብ19 09 ዓ/ም ተወለዱ በመጀመሪያ አማርኛና ንባብ ተምረው ዳዊት ደግሞ ከአለቃ ጎሩይ ከተባሉት ተማሩ ።

የዜማ ትምህርታቸውንም ከአለቃ ዘወልደ ማርያም ከተባሉት ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ ፤ የቅኔ ትምህርት ጎጃም ክፍለ ሀገር ድማ ጊዮርጊስ ፤ ከአለቃ ወልደ ኪዳን ተምረው አጠናቅቀዋል ።

ቀጥለውም አቋቋም በጎንደር በዓታ ከመምሕር ክፍሌ ዘንድ ተምረዋል ፤ መጻሕፍት ሐዲሳትንም ጎንደር ከተማ ከመምህር ታዬና ከመምህር ምሕረቱ ዘንድ ተምረዋል ። የቅዳሴ ትምህርትንም መምህር ማህሉ ከተባሉት ዘንድ ስለልኩላ ተምረው ተመርቀዋል ። በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም ከጎንደር ወደ ሸዋ በመምጣት መንበረ መንግሥት ገብርኤል ሦስት ዓመታት ሙሉ መጻሕፍተ ሐዲሳትን አስተምረዋል ። በዚህ ቦታ ላይ አስተምረው ካስመረቋቸው መካከል ፀባቴ ክፍለ ዮሐንስ ዛሬ አቡነ ጴጥሮስ ይገኙበታል ።

በ፲፱፻፶፪ ዓ/ም ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ሔደው መጻሕፍተ ሐዲሳትን በማስተማር እስካሁን ድረስ በዚሁ የመምህርነት ተግባር ላይ ይገኛሉ ። ፫ ዓመት በመንበረ መንግሥት ቅ/ገብርኤል ፳፯ ዓመታት በደብረ ሊባኖስ ገዳም በጠቅላላ ፴ ዓመታት የሐዲስን ጉባኤ ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው አሁንም በማገልገል ላይ ይገኛሉ ። በነዚህ በ፴ ዓመታት ውስጥ መምህር ብርሃኑ ወ/ሥላሴ አስተምረው ካስመረቋቸው መካከል አባ ዜና ዛሬ አቡነ ዜና ማርቆስ የፓትርያርኩ ረዳት ሊቀጳጳስና የቅዱስ ጳውሎስ ክፍተኛ ት/ቤት ዲን አባ ስብሐት ዛሬ አቡነ ዘካርያስ እነዚህ ከጳጳሳት መካከል የሚገኙት ሲሆኑ ሌሎች አባ መዘምር ተገኝ የየካ ደብረ ማህሌ ቅ/ሚካኤል ቤ/ክ አስተዳዳሪ መልአከ አሚን አባ ዘካርያስ ኃ/ማርያም በደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤ/ክ አስተዳዳሪ ይገኙበታል ።



መ/ብርሃኑ ወ/ሥላሴ

አባ ኪዳነ ማርያም ወሎ የሚያስተምሩ በመምህርነት ተመርቀው መጻሕፍተ ሐዲሳትን የሚያስተምሩ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ውስጥ መሪ ጌታ ገብረ ሕይወት ገብረ ኢየሱስ ፡ መሪጌታ በቃለ ኃይሉ ተምረው ተመረቁ መምሕር ብርሃነ ሕይወት ሐረር የሐዲስ መምህር ሆነው የሚያስተምሩ እነዚህ ሲሆኑ ሌሎች በስብከተ ወንጌል ተደልድለው ያስተምራሉ ። ከነዚህ መካከል መሪጌታ ደባቤ መልአክ በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሚሠሩ ይገኙበታል ሌሎችም ብዙዎችን አስተምረዋል ።

በአሁኑ ጊዜ መምህር ብርሃኑ የሚያስተምሩት በደብረ ሊባኖስ በመምህር ገብረ ኢየሱስ ስም በተቋቋመው ቤተ ተክለ ሃይማኖት ት/ቤት ውስጥ ነው በዚህ ትምህርት ቤት የሐዲሱን ጉባኤ እርሳቸው ይመራሉ ፤ በትምህርት ቤቱ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ በሐዲስ ትምህርት ቤት የሐዲሱን የሚሳተፉ ፲፩ ተማሮች ይገኛሉ ። እነዚህ ተማሮች በመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽ/ቤት ሥር አዳሪ ሆነው የሚማሩ ሲሆኑ ፤ ድርጎ ከገዳሙ ሊያገኙ የሚችሉት በመደበኛ ሳይሆን ገዳሙን በሞያቸውና በመንፈሳዊ ትምህርት የሚያገለግሉ ብቻ ናቸው ።

ሐዲስን ተምሮ ለመመረቅ የሚያስችለው ስንት ዓመት እንደሆነ ተጠይቀው በሰጡት መልስ እንደተማሪው ትጋት እንጅ ጊዜ አይወስንም ነበር ፤ አሁን ግን በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት ለሐዲስ ፮ ዓመታት ለብሉይ ፳ ዓመታት ከተከታተሉ በኋላ በሁለተኛ ደረጃ ብቁዕነትን በሚመለከት የምስክር ወረቀት ይሰጣል ይኸውም 1ኛ ለሐዲስ መምህርነት የሚያበቃው በመመዘኛ ነጥብ ሲመረጥ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለስብከተ ወንጌል የሚያበቃውን ማዕርግ ይገኛል ።

ይህ የአሁኑ የቅ/ሲኖዶስ ለትምህርቱ የጊዜ ገደብ መስጠት በጣም ጠቃሚ ይሆናል ብዬ የምገምተው ቀድሞ እስከ ፲፭ ዓመታት የሚቆዩ ይገኙ ስለነበር ሊያተጋቸውና ለትምህርቱም ውድድር ለመክፈት ፈጣን ርምጃ ለማስገኘት ያስችላል እላለሁ ።

በአሁኑ ጊዜ ትምህርቱ የሚሰጠው ከጥዋቱ ፫ ሰዓት ፱ መሆኑን ገልጸውልናል ። ከዚያ በኋላ ግን ዕረፍት ይሆናል ብለዋል ግን ለተማሮችም ሆነ ለመምህራን ይህ ዓይነት ያለ ዕረፍት እስከ ፱ ሰዓት ሙሉ መማርም ሆነ ማስተማር

www.ethiopianorthodox.org

# ሌሊት በመማር ቀን ማስተማር

ዕድሜ ቀስበቀስ ተሰባስቦ በቅፅበት የሚፈታ አፍላ ገበያ ነው ፡፡ ዘመን ያፈራውንና ወቅት ያነግሠውን የምድር በረከት ሁሉ እንደየፍላጐቱ ለማዳረስ ልውውጥ የሚደረገው በደጋ አካባቢ የሚበቅለውን ለቆለኛው የበርሐውን ውጤት ደግሞ ለደገኛው ለማቀበል ሰዎች የልውውጥ ፍላጐታቸውን የሚያከናውኑት ገበያ በተሰኘው ነፃ መድረክ ነው ፡፡

የገበያን ጠባይና ይዘት ስንመለከት በወቅት የሚሠራ ፡፡ አዋጅ ሳይነገር ሰዓቱን ጠብቆ የሚፈታ ቢበዛ የግማሽ ቀን ዕድሜ ያለው ለመሆኑ በአብዛኛው የሀገር ልውውጥ ልምድ ይታያል ይልቁንም በከተሞች አካባቢ ቀደም ሲል በልማድ የቆየውን የገበያ ይዘት የሚለውጡና ባሕሉን የሚያዛቡ ዘለዓለማዊ አስመስሉ የሚያሳዩ የስም ገጸ በረከት ሰተውት ይታያሉ ፡፡ ብሉም "ስም ወደ ሥራ ያመራል" ተብሎ እንደተነገረው ሰዓትና ወቅት የማይወስነው ለማለት ጉልት የሚል ስም ተሠጥቶት ከቀኑ አንድ ሰዓት እስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት ሲሠራበት ይታያል ፡፡ ቢሆንም በተወሰነ ጊዜ የሚፈታ ወቅታዊ ገበያ መሆኑ አያጠራጥርም ፡፡

ታዲያ ገበያ ወቅታዊ መሆኑን የተረዱ ሰዐት ያልፋቸው ለመጠቀም ቀን ከሌሊት ደክመው በያዙት ያጡትን ለውጠው ለማግኘት የሚጥሩ ጥቂቶች አይደሉም በመፋጠናቸውም ብዛት ያጡትን ያገኛሉ ፡፡ የሚሹትን ሁሉ ባላቸው ላይ ለመጨመር አመች ጊዜ ያገኛሉ ፡፡ ገበያ ከተፈታ የሚደርሱ ሰነፎች ግን ምንኳንስ ያጡትን ሊያገኙ ተሸክመው ሂደው ተሸክመው በመመለስ ትርፋቸው ብቻ ድካም ከመሆን በስተቀር ፋይዳ አይኖራቸውም ፡፡

እንግዲህ ገበያ ለተወሰኑ ሰዓታት በደግቅ ሁኔታ ተሰባስቦ ከተወሰነ ፡ ሰዓት በኋላ ደግሞ እንዳልነበረ የሚበተን እንደሆን ሁሉ የሰው ልጅ ዕድሜም በዓለመ ሥጋ የተወሰነ መሆኑንና አንድ ቀን በሞት ጥላ ሥር እንደሚጠለል ለመገለፅ ነው ፡፡

ሰው በመዋዕለ ዘመኑ የማያልፍ ሥራ ሠርቶ ለትውልድ የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት ኃላፊ (ሟች) ፍጡር እንጂ በሚታየው ዓለም ቋሚ ሁኖ ዘለዓለም የሚኖር መልዕልተ ፍጥረት አይደለም ስለሆነም የሰው ዕድሜ በአጀንዳ ተወስኖ የተያዘና በቀጠሮ ታውቆ የሚጠበቅ ሳይሆን ከእሉበት ቅፅበት ጀምሮ ጊዜ ሳይወስኑ ቀንና ሌሊት ተሯሩጦ መሥራትንና የታሪክ ባለቤት ለመሆን መጣርን ይጠይቃል ፡፡

ዓለም ከደረሰበት ለመድረስ ፡ መርምሮ ያገኘውን ምሥጢር ለመረዳት ፤ የተሠወረውንም አውጥቶ ለማሣወቅ ፤ ብሎም ለሰው ልጅ ቀዋሚ ጥቅም ሠጭ እንዲሆን ለማድረግ መማር አስፈላጊ ነው ፡፡ መማርም ብቻ ሣይሆን የተማሩትን ማስተማር ፤ ያወቁትንም ላላወቁት ማሳወቅም ሰብአዊ ግዴታ መሆኑ ይታመናል ፡፡ ለዚህ መልካም ሩጫና በጉ ጥረት ለመፍጠን ደግሞ ጊዜ አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም ፡፡ ነገር ግን ጊዜ በወቅቱ ሲሠሩበት እንጂ ተፈልጐ የሚገኝ ካለፈ በኋላ ቆየኝ ቢሉት ቋሞ የሚጠብቅ አለመሆኑ ሌላው ችግር ይሆናል ፡፡ ለዚህም ነው ደራሲው "ጊዜ ታክሲ አይደለም አይጠብቅም ቋሞ ካልተሣፈሩበት ቶሎ ተሽቀዳድሞ" በማለት በብዕራቸው የሰበኩት ፡፡ በዚህ ምክር አዘል አነጋገር ሁላችንም እንደምንስማማ ከልብ እተማመናለሁ ፡፡

ለመማርና ለማስተማር የሚደረገውን መሯሯጥ በዘመናችን ስንመለከት ይህን ጥቅስ ትውልዱ በጥብቅ የተረዳው ለመሆኑ አያጠያይቅም ፡፡ ይልቁንም ጉልህ ማስረጃው የሁለተኛ አጠቃላይ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው በሥራ ላይ የሚገኙ ሠራተኞች ራሳቸውንና የሥራ ይዘታቸውን ለማሻሻል በሚያደርጉት ጥረት ቀን ሥራቸውን ሲሰሩ ውለው ማታ ደግሞ ወደ ት/ቤት ሲገሠግሱ መታየታቸው ነው ፡፡ በዚህ ሁኔታ የሕሊና ዕረፍት ሳይሻ ቀን በማስተማር ሌሊት ደግሞ በመማር ተጠምዶ ዲፕሎማ ያገኘው ለዲግሪ ባለዲግሪው ደግሞ ዶክትሬት ለመድረስ ባለው ጽኑ ፍላጐት ጊዜውን በከንቱ ላለማባከን የሚያደርገው መሯሯጥና በወሰነ ዕድሜው ለመጠቀም የሚያሳየው ያላሰለሰ የቀን ተሌት ጥረት ይበል ያሰኛል ፡፡

በመዋዕለ ዘመን ለመጠቀም የሚደረገው የቀን ከሌት ጥረት ጊዜ መቶጠቡም በላይ "ጊዜ ከሚሠራብህ ሥራበት" የሚለውን የፍልስፍና ንግግር ሙሉ በሙሉ በሥራ የተረጐመ በመሆኑ ደስ ከማሰኘትም አልፎ ለሰው ልጅ የአእምሮ እና የኑሮ መሻሻል ለሀገርም ዕድገት የወደፊት ጽኑ መሠረት ነው ፡፡ ታዲያ ይህ የሕሊና ደወል በሁላችንም አእምሮ መጮኽ የሚገባው ዓቢይ መልእክት መሆን አለበት ፡፡

በተለይ ጥንታዊውን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ስንመለከት ጊዜን ለመቆጠብና ሳይባክን ለመጠቀም በማስተማር ዓለም የሚዋኘው መምህርም ሆነ ተማሪ የማስተማርና የመማር ፕሮግራማቸውን በሁለት ክፍለ ጊዜያት ከፍለው ሲጠቀሙ ይታያሉ ፡፡

ማለትም ዓይን በማይባክንበት አእምሮ በሚሠበሰብበት ሰዓተ ሌሊት የቃል ትምህርቱን ሲማር በማንበብና ልዩ ልዩ የዜማ ምልክቶችን በማየት በዜማ ጩኸት ለመማር የሚያስችለውን ትምህርት ደግሞ ቀን በተፈጥሮ የፀሐይ ብርሃን እየተረዳ ይማራል ፡፡ በዚህ ሁኔታ ብዙ ዘመን ይጨርስበት የነበረውን ትምህርት በአጭር ጊዜ አጠናቶ መምህር ይባልና ተረፈ ዘመኑን ለማስተማር ያውለዋል ፡ መምህር ከተባለ በኋላ ያላወቀውን ከመማር አይቦዝንም ከተማሪዎቹ መካከል እርሱ በሚገባ ያላወቀውን የትምህርት ዓይነት ጠለቅ አርጐ የሚያውቅ የተማሪ መምህር ሊኖር ስለሚችል ለተማሪው የእርሱን ሙያ እያስተማረ ከተማሪው ደግሞ የሚፈለገውን ለማወቅ ይማራል ፡፡ በዚህም ይዞታ ከጊዜ ወደ ጊዜ በእውቀት እየጐለመሰ ይሄዳል ፡፡

በጽሑፋችን ርእስ የጠቀስነው ግን ከዚህ ለየት ያለው የአንድ ሰው ታሪክ ይሆናል ፡፡ የዚህ ሰው ስም ኒቆዲሞስ ነው ኒቆዲሞስ በተለያዩ ሦስት ነገሮች የታወቀና ስመ ጥር ሰው ነበር ፡፡ ከሚታወቅባቸው አንዱ በኦሪት ትምህርቱ ሲሆን ሁለተኛውም የአይሁድ ሹም በመሆኑና ሦስተኛ በባለጸጋነቱ ይታወቅ ነበር ፡፡

ይህ ሰው ትምህርተ ኦሪትን ማለትም የሙሴን ሕግ ጠንቅቆ ያውቅ የነበረ ምሁረ ኦሪት ሲሆን ኦሪትንና ነቢያትን ለመፈጸም የመጣው እግዚአብሔር ወልድ ክርስቶስ ሥጋ ስብእን ለብሶ በሚያስተምርበት ወቅት ዕድል ገጥሞት የታሪካ ሰው ለመሆን በቅቷል ፡፡ ኒቆዲሞስ ከአይሁድ ወገን የሆኑ ሁሉ የክርስቶስን ትምህርት እንዳይሰሙ ካህናተ አይሁድ ውሳኔ ሰጥተው በነበረበት ጊዜ ውሣኔውን አእምሮው ሊቀበልለት ባለመቻሉ የክርስቶስን ጣዕመ ትምህርት ለመቅመስና በእርሱም ለማመን አመች ጊዜና ሁኔታ ይመርጥና ያደላድል ይፈልግ ነበር ፡፡

ምክንያቱም ቀን ከክርስቶስ ዘንድ ሲማር ቢታይ ውሣኔ አይሁድን ሽሮ ስለተገኘ ከማኅበራቸውና ከሥልጣኑ ይለዩታል ፡፡ ተከብሮ ከኖረበት ክብሩ ያዋርዱታል በሌላም አንፃር እስከ አሁን ትምህርት አላልቅለት ብሎ ይማራል በሚል ይንቁኛል ከሚል ሥጋት የተነሣ ከጽኑ መዋግደ ሀሳብ ወድቆ ሳለ ወደ ክርስቶስ የሚደረስበትን አማራጭ አገኘ ያገኘውም ዘዴ ቀን ሥራውን በመሥራት ከአይሁድ ማኅበር አለሁ እያለ ሌሊት ወደ ክርስቶስ ሂዶ ትምህርቱን መስማትና ተአምራቱን ማየት በመሆኑ ከማንም አስቀድሞ ሌሊት ኒቆዲሞስ ወደ ክርስቶስ መጥቷል ፡፡

ወደ እርሱ ቀርቦም "መምህር ከእግዚአብሔር አካል ዘእም አካል ፡ ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወልደህ ልታስተምር እንደመጣህ እናውቃለን ፡፡ በሕልውናው ከእርሱ ጋራ ካለህ ከአንተ በስተቀር አንተ የምታደርገውን ታምራት ሊያደርግ የሚቻለው የለምና" በማለት ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ መሆኑን መስክሮ ሰገደለት ዮሐ.፫.፩-፳

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም "እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ሁለተኛ ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይቻለውም ፡፡ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነውና ፡፡ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው" ሲል ሰው የእግዚአብሔር ልጅ የሚሆንበትን ምሥጢር ገልጾ አስተምሮታል ፡፡ ኒቆዲሞስ በዚህ ጽኑ ተስፋ ተመስርቶ ቀን በማስተማር ሌሊት በመማር የሁለቱም ዓለም ባለጸጋ ለመሆን በቃ ፡፡ አቋሙም የተስተካከለና የማያወላውል ጽኑ ሆነ ፡፡ የክርስቶስን ትምህርት በጆሮው ሰምቶ ተአምራቱን በዓይኑ አይቷልና ፡፡ በመጨረሻ ክርስቶስ የሞት ፅዋን በቀመሰባት ሰዓት የመከራ ዘመድ ሁኖ ቀርቧል ፡፡ ዮሐ. ፲፱-፴፱ ፡፡

ማንም ሊቀርብ ባልደፈረበት ጊዜ ወደ አይሁድ በግልጽ ቀርቦ የክርስቶስን ሥጋ እንዲሠጡት ጠየቀ ፡፡ ከፈቀዱለት በኋላም ወስዶ ከዮሴፍ ጋር ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት" በማለት የማይሞት ዘለዓለማዊ አምላክ መሆኑን መስክሮ ሥጋውን በክብር ገንዞ ቀብሯል ፡፡ እንግዲህ የኒቆዲሞስ ግመንና መታመን በመጨረሻ በጉልህ ተገልጧል ፡፡ እኛም ቀን በተመደብንበት ሥራ ስንሠራ እየዋልን በትርፍ ጊዜያችን ተግተን ብንማር ከፍ ያለ ዕውቀትን ለመገብየት እንችላለንና የዕረፍት ጊዜያችን በቁም ነገር እናሳልፈው ፡፡

አባ ብርሃን መስቀል ጎየሁ

---

መሰልቸትን አያስከትልም ወይ ለተባሉት ሲናገሩ ፡ ርግጥ ያሰለቻል ፡፡ አሁን ግን አዲስ ፕሮግራም ወጥቶ በሥራ ላይ እንደሚውል የሚጠበቅ አለ ይኸውም ከጥዋቱ ፲፪ ሰዓት ጸሎተ ማሕበር በ፩ ሰዓት ቁርስ ከሁለት ሰዓት እስከ ሰባት ትምህርት ተካሂዶ በሰባት ሰዓት ምግ ፤ ከሰዓት በኋላ ከ፱ እስከ ፲፩ ሰዓት ትምህርት እንዲሰጥ መታቀዱን ገልጸው ይኸውም ቢሆን ለገዳማዊ ሥርዓት እንደማያመች መምህር ብርሃኑ ይናገራሉ ፡፡ ምክንያቱም ገዳሙ በአለው መንፈሳዊ ሥርዓት እስከ ፱ ሰዓት መቆየት ግዴታ ነው ፤ ይህ የማይሆነው ቅዳሜና ዕሁድ በዓለ ሃምሣ ፡ ልደትና ጥምቀት ብቻ እንጂ ቅዳሴው ውሉ ነው ብለዋል ፡፡

እስካሁን በርሳቸው በኩል በልዩ ልዩ የመንግሥት መ/ቤት እና በሌላም በኩል ተመርቀው በልዩ ልዩ ሥራ ላዩ የተደለደሉ ይገኛሉ ብለዋል ፡፡

የዜናው አቅራቢ ሐፈ ወርቅ አሰግድ

---

# ክርስቲያናዊ - ሕይወት

ከገጽ ፲፫ የዞረ

ራት የማይችለውን ሁሉ መቁረጥና ወደ ማይጠፋ እሳት መጨመሩም ስለማይቀር ካሁኑ መልካም ፍሬን ማፍራት የሚችልበትን ንስሐ መግባት የያንዳንዱ ክርስቲያን ግዴታ ነው ፡፡

በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገቡትን አምላካውያት ቃላት ሰምቶ እንዳልሰሙ ማለፍም መቅሠፍትን ይጨምራል" የጌታውን ትእዛዝ እያወቀ የማይፈጽም መቅሠፍቱ ብዙ ነው ተብሏልና ፡፡

መምህር ሀብተ ማርያም ተድላ





www.ethiopianorthodox.org

# የጨንቻ ማሠልጠኛ ፶፪ ካህናት አስመረቀ

በጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት በጎፋ አውራጃ በጨንቻ የተቋቋመው የካህናት ማሠልጠኛ ተቋም ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አለቃ መኰንን የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ በጨንቻ የአድባራት አለቆችና ጥሪ የተደረገላቸው የከተማው ነዋሪዎች በተገኙበት ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ፶፪ የሚሆኑ ካህናት ማስመረቁን የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ገለጸ ።

ካህናቱ ፩ኛ ከመስከረም ፩ እስከ ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ፪ኛ (ከየካቲት ፩ እስከ ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ድረስ የሠለጠኑ መሆናቸውን ሀገረ ስብከቱ ገልጾ በአንደኛ ዙር የሰለጠኑ ሃያ አምስት በሁለተኛ ዙር ፳፯ በጠቅላላ ሃምሳ ሁለት ካህናት መሆናቸውንም

ጨምሮ ገልጾአል የትምህርቱንም ዓይነት ሲያስረዳ ፣

ሀ የነገረ መለኮት

ለ/ ቅዳሴ

ሐ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

መ የስብከት ዘዴ

ሠ/ ምሥጢረ ቤ/ ክርስቲያን

ረ/ ፀዋትወ ዜማ

ሰ/ ሰበካ ጉባኤ

በልማትና በመሳሰሉት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት አሰልጥኖ ማስመረቁንና የምስክር ወረቀቱንም በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ ዘካርያስ እጅ ከላይ በተጠቀሰው ዕለት የተሰጣቸው መሆኑን በዝርዝር አስረድቶአል ።

ሀገረ ስብከቱ ጽሑፉን በማራዘም ሲያትት ለበዓሉ በወጣው መርሐ ግብር መሠረት በሰልጣኞቹ ትምህርት አዘል ከመጽሐፍ ቅዱስ የተዘጋጁ ድራማዎች በመታየቱ ተመልካቹን ሕዝብ የመንፈስ ርካታን እንዲያገኝ አድርጎታል ካለ በኋላ ከድራማው ፍጻሜ ቀጥሎ ሊቃውንቱ በየተራ ከብፁዕነታቸው ፊት እየቀረቡ የተለያዩ ቅኔዎችና የአማርኛ ግጥሞች አበርክተዋል ብሎአል ። ዜናው በተጨማሪ ሲያብራራም፡-

የምስክር ወረቀቱና የሽልማቱ ሥነ ሥርዓት እንዳበቃም ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ለተመራቂዎቹ ትምህርትና መመሪያ ሰጥተዋል ብሎ ብፁዕነታቸው "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ" በሚለው ቃል ተነሥተው መማር ብዙ በረከትና ጸጋ የሚገኝበት ፍቱን ሀብት መሆኑንና ሠልጣኞቹም በዚሁ ማሠልጠኛ በርከት ላሉ ወራቶች ሲቆዩ የአእምሮ ስፋትና የትምህርት ምርምር ጥልቀት እንዳገኙ አውስተው በሚማሩት ትምህርትም እጽፍ ድርብ መክሊት እንደሚያፈሩበት የታመነ መሆኑን ካስገነዘቡ በኋላ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካህናትን በጨው መስሎ መናገሩ ከሌላው ይልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ለማጠየቅ ነው በማለት አስረድተዋል። ይህንኑም በበለጠ እንዲረዱት የጨው ጠባይ ከካህናት ሥራ ጋር በማዛመድ እያብራሩ ጠቃሚ ትምህርትና መመሪያ የሰጡ መሆናቸውን የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ባስተላለፈው ዘገባ አረጋግጧል ።

ከዚህም ሌላ በማሠልጠኛው ርእሰ መምህር በአቶ እሸቴ ተ/ሥላሴ ለእለቱ የተዘጋጀ አጭር ንግግር የተደረገ መሆኑን ከጽ/ቤቱ የደረሰን ዘገባ ያረጋግጣል ፤ በመጨረሻም ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ቡራኬ ሰጥተው እንዳበቁ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ። ሲል ሀ/ስብከቱ ዘገባውን ደምድሞአል ።

ከተደረጉት ቅኔዎችና ንግግሮች መካከልም የአማርኛው ግጥም ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቦአል ።

እስቲ በስመ አብ ብየ ልጀምር ሰላምታ
ለቸሩ ፈጣሪ ለላይኛው ጌታ ።
እናንተ ካህናቱ ስሙኝ ልንገራችሁ
ስብከተ ወንጌልን አስፋፉ እባካችሁ
በስብከተ ወንጌል ይታነፅ ቤታችሁ
ስብከተ ወንጌል ነው ዘለዓለም ተስፋችሁ
ሰበካ ጉባኤን የሚያስፋፋላችሁ ።
ሰበካ ጉባኤን የሚያስፋፋ ምዕመን
በላይኛው ቦታ ምንም አይኰነን ።
መንግሥተ ሰማያት ከተከፈተማ
ፈጽሞ ይዘጋል የሲኦል ከተማ ።
የሲኦል ጨለማ ከጠፋልን በውነት
የአዳም ልጆች ሁሉ እንገባለን ገነት ።
ገነት ለኛ ሆና ከተሰጠችን
ሰበካ ጉባኤን እናድናለን ።
ሰበካ ጉባኤን ፀንቶ ያስተማረ
ዘላለም ይኖራል እንደተከበረ ።
ጨንቻ ማሠልጠኛ በጣም ደስ ይበልሽ
የዕውቀትን ገበያ ገበዩ ልጆችሽ
ዕውቀት አዝመራችን በረዶ ያልመታው
ጎተራው ተጨንቆ ቤታችንን ሞላው ።
በዚች ማሠልጠኛ የተማረ ሁሉ
ዞሮ ማስተማር ነው በዱር በገደሉ ።
በዱር በገደሉ ዞረን እናስተምር
የተማርነው ትምህርት ምንም አያሳፍር
ጥበብ ቤቷን ሠራች በካህናት ዘንድ
አቁማለችና ሰባቱን አዕማድ ።
አቋቋም ተምሬ በጣም ደስ ብሎኛል
እስመ ላለም ይገ አቡኑ ቀርቶኛል ።
ነገረ ሀላዌን ወደጐን ትቶ
መቀመጥ ይሻላል ካቡን ተጠግቶ
መሔድ ይሻል ነበር በተቃናው መንገድ
አሁን ምን ያደርጋል ካቡን ጥሶ መሄድ
እንጨቱን ገደሉን መጠጋቱን ትቸ
ሲደክመኝ አርፋለሁ ካቡን ተጠግቼ ።
እንማር ብሉይን ደግሞም ከሐዲስ
ከወንጌሉ መሪ ከዘካርያስ
ብሉይና ሐዲስ በጣም ከተማርን
እኛም ለማስተማር እንችላለን ።
ስብከተ ወንጌልን ምእመን ከጨበጠ
ሰበካ ጉባኤ በታሪክ አጌጠ ።
በትምህርት ቤቶች አጊጦ ሰፈራው
አብቦና አፍርቶ ይታያል ይኸው ።
ጨንቻ ማሠልጠኛ ከሁሉ በለጠች
በታላላቅ ሰዎች ይኸው ተጎበኘች ።
ያደረሰን እኛን ለበዓላችን
ለሁሉ ፈጣሪ አምላክ ይመስገን ።

መሪጌታ ጀምበሬ አዳነ
የመንፈሳዊ ትምህርት መምሕር ።



# ክርስቲያናዊ ሕይወት

ነቢዩ ኢሳይያስ ከጌታ ልደት በፊት ወደ ሰባት መቶ ዓመት የነበረ ታላቅ ነቢይ ሲሆን መጥምቁ ዮሐንስ ስለሚያስተምረው የሰው ልጆች እኩልነት በመንፈሰ ትንቢት ሲናገር የአዋጅ ነጋሪ ቃል የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ ፣ የአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ ፤ ሸለቆው ከፍ ይላል ፣ ተራራና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል ፣ ጠማማውም ይቃናል ፣ የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል ። በማለት ተናገረ ። ኢሳ ፵፡፫-፭ ።

ጊዜውም ሲደርስ አዋጅ ነጋሪ ተብሎ ትንቢት የተነገረለት መጥምቁ ዮሐንስ በይሁዳ ምድረበዳ በዮርዳኖስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ መልእክቱን ማስተላለፍ ጀመረ

ይህን ትምህርቱን የሰሙ የኢየሩሳሌምና የይሁዳ እንዲሁም በዮርዳኖስ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ወደ እሱ እየመጡ የንስሐ ጥምቀት ይጠመቁና ይማሩ ነበር ።

ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንም እሱ ወደሚያስተምርበትና የሚያጠምቅበት ቦታ ሲመጡ አየና "እናንተ የእባብ ልጆች ከሚመጣው መቅሠፍት ፈተናና መዓት ታመልጡ ዘንድ ማን አመለከታችሁ ? እንግዲያውስ ከእንግዲህ ወዲህ ለንስሐ የሚያበቃችሁ መልካም ፍሬ ይኑራችሁ ። ይህ ካልሆነ አብርሃምን ያህል አባት አለን በማለት የምታመልጡ አይምሰላችሁ።እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች የአብርሃም ልጆች አድርጎ ማስነሣት እንደሚችል ። እነግራችኋለሁ ካላችሁና ካስጠነቀቃችሁ በኋላ " ናሁ ወድአ ማሕፀ ውስተ ጉንደ ዕፀው ይንበር/ እነሆ ምሳር በዛፎች ግንድ ላይ ተቀምጧል ፤ ለመቁረጥ ተዘጋጅቷል/ ፤ መልካም ፍሬ የማያፈራውን ዛፍ ሁሉ ይቆርጡታል ፤ ከእሳትም ይጨምሩታል" በማለት ሁሉም በእኩልነት ንስሐ እንዲገቡና የክርስቶስን አምበዚህም አያይዞ "እኔ ለንስሐ እንዲጠቅማችሁ በውሀ አጠምቃችሁአለሁ፤ ጫማውን መሸከም የማይቻለኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል ። የእህሉን አውድማ የሚያጠራበት መንሽ በእጁ የያዘ ነው ፤ ስንዴውን ከጐተራው ውስጥ ይከትታል ፤ ገለባውን ግን በእሳት ያቃጥለዋል ብሏቸዋል ።

እንግዲህ ከላይ ያሠፈረውን መልእክት በዓይነ ሕሊና ተመልክተን ብንመረምረው ብዙ ጥቅም እናገኝበታለን ።ክርስቲያናዊ ሕይወትን ለመኖርም ጥሩ መመሪያ ይሆንልናል ።

ኃዋጅ ነጋሪው ፣ "የእግዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ" ሲል ምን ማለቱ ነው? እግዚአብሔር ወዴት ሊጓዝ ፈልጎ ይሆን? የሚጠረገውስ መንገድ አስፋልት ወይስ የጠጠር ? ነቢዩ ይህን የተናገረው ምን ለማለት ፈልጎ ይሆን ?

ልዑል እግዚአብሔር ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ? ብሎ የሚዘምትበት የተለየ ጠላት ኑሮት ቢዘምት ከመንገድ እሾህ እንዳይወጋውና እንቅፋት እንዳይመታው ታስቦ የተነገረ ቃል የሚመስለው የዋህ ይኖር ይሆን ? መኖር የለበትም እሾሁ እንቅፋቱ በትዕቢት የተወጠረ ፤ በተንኮል በምቀኝነት ፣ በሐሰት በማጭበርበር የተበከለ የያንዳንዳችን የሰዎች ልቦና መሆኑን አስቀድሞ መገንዘብ ያስፈልጋል ።

የልዑል እግዚአብሔር ዘመቻ ከማኅበረ መላእክት ተለይቶ የጠፋውን የሰውን ልጅ ፍለጋ ስለሆነ መንገዱ መግቢያ ቢሩም ራሱ የሰው ልጅ ልቡና በመሆኑ ጠማማና ዓመፀኛ ሕሊና ያላቸው ወደቅንነት እንዲመለሱ ፣ ትዕቢተኞች ከእኛ በቀር ማን አለ ? ብለው በትውልድ ሐረጋቸው በማዕረግ ክፍተኛነታቸውና በልዩ ዕውቀታቸው የሚመኩና የተፈጥሮ ወንድማቸውን የሚንቁና የሚያቃልሉ ሁሉ ይህን መጥፎ አድራጎታቸውንና አስተሳሰባቸውን ትተው በንስሐ እንዲመለሱ ፤ የታነቁና የተዋረዱ የተጨቆኑና የተጠቁ ሰብአዊ መብታቸው ታውቆላቸው እንዲስተካከሉ በመንፈስ እግዚአብሔር የተነገረ ትእዛዝ ነው ።

መጥምቁ ዮሐንስ "እኔ የማጠምቃችሁ ለንስሐ በውሀ ነው ፤ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል "ማለቱም የዮሐንስ ጥምቀት ማንኛውም ሰው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት በንስሐ ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅ እንጂ ልጅነትን የሚያስጥ ባለመሆኑ " ተዘጋጅታችሁ ንስሐ ገብታችሁ ጠብቁ የአብርሃም ልጆች ነን በማለት ማምለጥ የምትችሉ አይምሰላችሁ ፤ አብርሃምን በምግባሩ ካልተከታተላችሁት ዘር በመቁጠር የአብርሃምን ርሥተ መንግሥተ ሰማያት መውረስ አትችሉም ።

ልዑል እግዚአብሔር ከእነዚያ ከተናቁት ከአሕዛብ ወገን የአብርሃምን ልጆች አድርጎ በእምነት ሊያስነሣ ይችላልና በማለት ገልጾ በኋላዬ የሚመጣ የሚለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን " "በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል " ልጅነትን ይሰጣችኋል ፤ የእግዚአብሔር ልጆች ትሆናላችሁ መንግሥተ ሰማያትን ትወርሳላችሁ ሲላቸው ነበር ። በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ ስለማጥመቅ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፪ ቁጥር ፩ እስከ መጨረሻው መመልከት በቂ ይሆናል ።

ዐውድማውን የሚያጠራበት መንሽ በእጁ መያዙን ገልጿል ፤ ስንዴውን ወደ ጐተራ ይከትታል ፤ ገለባውን በእሳት ያቃጥላልም ብሏል ንስሐ ካልገባችሁ በእሳት ትቃጠላላችሁ ፤ ንስሐ ገብታችሁና ተዘጋጅታችሁ ከጠበቃችሁት ግን መልካም ስንዴ ናችሁና ርስተ መንግሥተ ሰማያትን ትወርሳላችሁ ፤"መንሽ" የሚለውም መለኮታዊ ስልጣኑን ነው ይኸውም ኃጥአንን ከጻድቃን ጻድቃንን ከኃጥአን የሚለይበት ሥልጣን አለው ማለቱ ነበር ።

እንግዲህ በያንዳንዱ የዛፍ ግንድ ሥር ያለው ምሳር መልካም ፍሬን ማፍ

ተከታዩን በገጽ ፲፩ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት ፡

## የሊቀ ኅሩያን ዓለሙ አራጋው አጭር የሕይወት ታሪክ

ሊቀ ኅሩያን ዓለሙ አራጋው ከአባታቸው አቶ አራጋው ለውጤ ከእናታቸው ወ/ሮ ምጥን እንግዳ በ፲፱፻፲ ዓ/ም በጎንደር ሀገረ ስብከት ጋይንት አውራጃ ስማዳ ወረዳ ቃጫና ደብረ ቤቴል ኢየሱስ ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወደ አርጋ ቅዱስ ሚካኤል ደብር በመሄድ መሪጌታ ቢያድጌ ከተባሉት መምህር ፊደል ጀምረው ንባብ አንብበው ዳዊት ከደገሙ በኋላ ከዚያው ግዕዝና ዜማ ተምረዋል ። ከዚያም ወደጉና ቅዱስ ሚካኤል ፡ ወደ ቤተ ልሔም ወዘተ እየተዘዋወሩ ፀዋትወ ዜማን በሚገባ ተምረው ሲያበቁ ወደ ወሎ ሀገረ ስብከት በመሄድ ሰቆጣ ዓምደ ወርቅ ቂርቆስ ቀደም ሲል የተማሩትን ፀዋትወ ዜማ ከማጠናከራቸውም ሌላ ቅዳሴና ሰዓታትም ተምረዋል ።

ሊቀ ኅሩያን ዓለሙ እንደገና ወደ ትውልድ ሀገራቸው ጎንደር ተመልሰው ስማዳ ወረዳ ደብረ ዕንቁ ማርያም ከመምህር ጌጡ ተሰማ ቅኔ ከእነአገባቡና እርባ ቅምሩ ተምረው በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል ፤ በተጨማሪም ከመምህር ጌጡ የዳዊት የውዳሴ ማርያም የቅዳሴ ማርያም የነገሥት የዳዊት ትርጓሜና ባሕረ አሳብን ተምረዋል ።

ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ወሎ ሀገረ ስብከት ሄደው ዋድላ ደላንታ በአባ ነአኩቶ ለአብ ደብር ከአለቃ መርዓዊ በተጨማሪ አገባብና የቅኔ መንገዶችን ጨምረው በማጥናት የቅኔ ሞያቸውን ካጠናከሩ በኋላ ወደ ስማዳ በመመለስ እጅኪዳን ምህረትና ጠዶየ መርቆሬዎስ ከመምህር ገብረ እግዚአብሔር የተክሌ አቋቋምን ተምረዋል ፤ ከዚያም ወደ ተወለዱበት ደብር ቃጨና ደብረ ቤቴል ኢየሱስ ተመልሰው ወንበር ዘርግተው ጉባኤ እስፍተው ማስተማራቸውን ቀጥለዋል ።

ሊቀ ኅሩያን ማስተማር የጀመሩት በ፲፱፻፴፱ ዓ.ም. ስለሆነ አሁን ፶ ዓመታቸው ነው በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ብዙ ደቀ መዛሙርትን አስተምረው አውጥተው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ከእርሳቸው ተምረው በማስተማር ላይ የሚገኙት መምህራን 30 ሲሆኑ ቅኔ እየተቀኙ አገባብና አርባ ቅምር ባሕረ አሳብና የቅዳሴ ማርያም



ሊቀ ኅሩያን ዓለሙ አራጋው



የውዳሴ ማርያም ትርጉም እያጠኑ የሚሄዱት ደቀ መዛሙርት ስፍር ቁጥር እንደሌላቸው ራሳቸው ሊቀ ኅሩያን ዓለሙ አራጋው ገልጸውልናል ።

ሊቀ ኅሩያን ዓለሙ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት በተባለው ቃል መሠረት በተክሊልና በቁርባን ወ ሮ የልፍኝ አካሉን አግብተው አምስት ልጆችን ወልደዋል ፤ ሊቀ ኅሩያን በንቃትና በትጋት ማስተማራቸው በሁሉም ዘንድ ስለታወቀላቸው ከ፲፱፻፸፩ ዓ.ም ጠዳ ህብር ፶ የወር ደመወዝ ስለተመደበላቸው ጉባኤያቸውን አስፋፍተው በማስተማር ላይ ይገኛሉ ።

በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም በኅዳር ወር ወደ አዲስ አበባ መጥተው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃድ ሊቀ ኅሩያን ዓለሙ ተብለው ተሠይመዋል ። ሊቁ ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ካበረከቷቸው ቅኔዎች ጥቂቶቹን ቀጥለን አቅርበናቸዋል ።

ጉባኤ ቃና ፡

ተክለ ሃይማኖት ዮሐንስ እንተ ንብረተ ገዳም
ኢይበልዕ እክለ እንበለ ጸሎት ወጾም

ትርጓሜ ፡

መኖሪያው ገዳም የሆነ ተክለ ሃይማኖት ዮሐንስ ያለጾምና ጸሎት በስተቀር እህልን አይበላም ማለት ነው

ዋዜማ ቅኔ ፡

ጸሎትከ ወምጽዋትከ ፡ ቅድመ አሐዱ አምላክ አዘከሩከ ገሃደ
ቆርኔሌዎስ ተክለ ሃይማኖት ዘሰሩ ሕከ እደ
ላዕለ ነዳያን ሕዝብ እንዘ ትሠርዕ ማዕደ
ወአመ አሐዝከ ወርቀ ኩሎ መንገዶ
ኢያትረፍከ ለዜና አሐደ

ትርጓሜው

ማዕድን ለችግረኞች ለመሥራት የስጦታ እጅህን የምትዘረጋ ቆርኔሌዎስ ተክለ ሃይማኖት ሆይ ! ጸሎትህና ምጽዋትህ ወደ አምላክ ደርሰው አሳሰቡህ መንገድ ስትሄድ ወርቅንም በያዝክ ጊዜ ለወሬ አንድም አላተረፍክ ማለት ነው ።

ሥላሴ ቅኔ ፤

ተክለ አብ መሶበ ወርቅ ፤ እንተ ውስቴቱ ኅብስተ መና ፡ ወዝንቱ
ኅብስት ወሀቤ ሕይወት ለኩሉ
ይቀርብ ለካህናቲሁ በሰማይ በላዕሉ
ወዓዲ በምድር በታሕቱ እስከ ይጸግቡ
እሉ እስመ ተባረከ በመስተሉ ወእንዘ
ሀሎ ብርሃን ምስለ ፀዳሉ በጊዜሁ መምህራን ይብሉ ።

ትርጓሜው

ለሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ መና በውስጡ ያለበት መሶበ ወርቅ ተክለ ሃይማኖት በሰማይ ለካህናት ይቀርባል ሁለተኛውም በምድር ያሉ ሰዎች በእርሱ ይጠግባሉ በመስተሉ ተባርከዋልና ። ብርሃን ከፀዳሉ ጋር ሳለ በጊዜው መምህራን ይመገቡ ማለት ነው ።

ዘይዕዜ ቅኔ

ተክለ አብ ጴጥሮስ ሕያወ ስም እመንፈስ ቅዱስ ወማይ አመወለድከ ሕዝበከ ።
መርቆሬዎስ ዘክፍለ ጎንደር በአማን ወልድከ እስመ አንተ ክመ ለትውልደ ትውልድ ዘመንከ እንዘ ምዕት ዓመት ምኑነ ልብከ ። በመንፈቀ አምሳ ዓመት ኢትስደኒ ትዮሜከ

ትርጓሜው

ስምህ ሕያው የሆነ ጴጥሮስ ተክለ ሃይማኖት ሆይ ከመንፈስ ቅዱስ ውሀ ሕዝቦችን በወለድክ ጊዜ የጎንደር ሊቀ ጳጳስ መርቆሬዎስ በውነት ልጅህ ነው ። ዘመንህ ለልጅ ልጅ የሚደረሳ ነውና መቶ ዓመት በልብህ የተናቀ ሲሆን በፊትህ በመቶ እኩሌታ በሚሆን አምሳ ዘመን አትወስነኝ ማለት ነው ።

መወድስ ቅኔ

እምቀዳማዊ አዳም እስከነ ይዕዜ ኢወለደት ወልደ ወላድ ኢትዮጵያ የምስ ወለደት ተክለ ሃይማኖት ኖትያ ውስተ ባሕር ሊቀ ጵጵስና ዘጸሎት ጌልያ ቅንዓት እስመ አሐዛ ለእንተ ወሊደ ስዕነት ወላድ እስክንድርያ

ለዓለም

ንዋየ እመ አቀበት በኢኮኖሚያ
ደቂቀ ዘወለደት አልሐቀት በንዋያ



ወእመ ለስሙ ዓባይ ተክለ ሃይማኖት ሰመየ ተፈሥሐ ልቡናሃ ለእመ ተክለ አብ እግዚእ ኃረየ

ትርጓሜው

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሊቀ ጵጵስና ባሕር የሚዋኝ እንደ ተክለ ሃይማኖት ያለ ልጅ አልወለደችም ወላድ እስክንድርያን ቅንዓት ያዘታልና ።

ለዓለሙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ገንዘብን ጠብቃ በመያዟ በገንዘቧ ልጆቿን አሳደገች ።

ተክለ ሃይማኖትም በስሙ ከፍ ስላደረጋት ልቡናዋ ደስ ተሰኘ ማለት ነው ሊቀ ኅሩያን ዓለሙ አረጋው በሊቅነታቸው ላይ ግጥም በጽንና ትሕትናን ደርበው የያዙ ትሑት በመሆናቸው በማነኛውም ዘንድ ተወዳጅነት ያላቸው ታላቅ ሊቅ ናቸው ።

ሊቁ ከቅኔው ሞያቸው ጋር አቋቋም አዋቂ በመሆናቸው የዓመት በዓል ከመድረሱ በፊት የክብረ በዓሉን ቀለም ለደቀ መዛሙርቶቻቸው በማስጠናት ክብረ በዓሉ እንዲደምቅና ቤተ ክርስቲያንም በሚገባ እንድትገለገል ያደርጋሉ ። በዚህም መልካም ሥራቸው በመደሰት በአካባቢያቸው የሚኖሩ ካህናት ምእመናን በኩሉም በሁሉም የተማሉ ሊቅ እያሉ ያመሰግኗቸዋል ።

ሊቀ ኅሩያን ዓለሙ አራጋውን ስለ ጉባኤያቸው ጠይቀናቸው ሲያብራሩ ማስተማር ከጀመርኩበት ዘመን ጀምሮ ጉባኤ ፈትቼ አላውቅም የተማሮችም ብዛት ከ300 በላይ የሚሆንበት ወቅት አለ ።

ወደፊት ግን ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የጎንደር ሀ/ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በተማሮች ላይ የሚደርሰውን የጤናና የልብስ ችግር በሰበካ ጉባኤ አማካይነት እንደሚያስወግዱልን ተስፋ እናደርጋለን ፤ ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅም በተማሪዎች የሚደርሰው ችግር ሁሉ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በኩል ፤ እንደሚወገድልን ተስፋ ስለሰጡኝ

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

የልማት ዓይነቱ ብዙ ነው ። ነገር ግን እኛ ሁልጊዜ የምንገልጸው የልማት ተግባር በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሆኖ በካህናትና በሰበካ ጉባኤ አባላት የሚከናወነውን ሲሆን ካህናት ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዕረፍት በሚሆንበት ጊዜ የሚሠሩት ተግባረ ዕድ የሚተከሉት ተክል ፤ የሚዘሩት ዘር ወዘተ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ልማት ይባላል ። እን

---

በጣም ደስ ብሎኛል በማለት ሊቀ ኅሩያን ዓለሙ አራጋው ንግግራቸውን አጠቃለዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሊቀ ኅሩያን ዓለሙ ያሉ ብዙ ሊቃውንት አሏት ነገር ግን በራሳቸውም ሆነ በተማሮቻቸው ላይ ብዙ ችግር ይደርስባቸዋል ፤ አንዳንዶቹ የሚደርስባቸውን ችግር ሁሉ በመቋቋም ወንበራቸውን ዘርግተው ጉባያቸውን አስፋፍተው በማስተማር ላይ ሲገኙ አንዳንዶች ግን ችግሩን መቋቋም እያቃታቸው ጉባኤያቸውን እየፈቱ ወደ ልዩ ልዩ ተግባር ተሠማርተው ይገኛሉ ፤

መምህራን ካላስተማሩ ተማሮች ካልተማሩ የቤተ ክርስቲያችን ሥነ ሥርዓት ተጠብቆ ሃይማኖታችን ጸንቶ ምግባራችን አምሮ ሊኖር አይችልም ሃይማኖታችን ተጠብቆ ለመኖር እንዲችል መምህራን ጠንክረው እንዲያስተምሩ ተማሮችም እንዲማሩ ምእመናን በሰበካ ጉባኤ እየተደራጁ የሚፈልጓቸውን ተቋጽኦ መክፈል አለባቸው ።

መምህራንም ቢሆኑ የሚደርስባቸውን ችግር ታግሦ የማስተማር ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ሊዘነጉት አይገባም። ሊቀ ኅሩያን ዓለሙ አራጋውን በመጨረሻ የምናሳስባቸው ምንም ችግር ቢደርስባቸው እንደ እስከ ዛሬው ወንበራቸውን ዘርግተው ጉባኤያቸውን አስፋፍተው በንቃትና በትጋት ከማስተማር ቶል እንዳይሉ ነው ። ቤተ ክርስቲያናችንም ለእብነት መምህራን እንክብካቤ እያደረገች ናት ።

ዜናውአቅራቢ ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ

ዲሁም አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን መሥራት ያረጁትን አብያተ ክርስቲያናት ማደስና የመሳሰሉት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን የልማት ሥራዎች ናቸው ።

ስለዚህ በዛሬው ልማት በቤተ ክርስቲያን በሚለው ዓምዳችን ለአንባብያን የምናቀርበው በሸዋ ሀ/ስብከት በሐይቆችና ቡታጅራ አውራጃ በሻሸመኔ ወረዳ በኩየራ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ስለተደረገውና ወደፊትም ሊፈጸም ስለታቀደው የልማት ተግባር እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኑን ለማሠራት ስለሚደረገው ዝግጅት ነው ።


ስለልማቱም ሆነ ስለቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ዝግጅት የጠየቅናቸውና ማብራሪያ የሰጡት የቤተክርስቲያኑ አሠሪ ኮሚ

ረቀ እንደሌለ በዓይናችን በማየት ተረድተናል ። አቶ ዓለማየሁ ካሳ ማብራሪያቸውን በመቀጠል

፪ኛ. የቤተ ክርስቲያኑን ዙሪያ በአጠናና በብረት ሽቦ አሳጥረናል ።

፫ኛ. በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ውጭ ፲ ጥንድ በሬ የሚያውል መሬት አርሠን ሥንዴ በመዝራት ሃያ ሁለት ኩንታል ሥንዴ አምርተናል ፤ ለቤተ ክርስቲያኑ አሥር ሄክታር መሬት ተጠይቆ እንዲሠጥ ከመንግሥት ስለተፈቀደ ያንን ከመንግሥት የተፈቀደውን መሬት ባገኘን ጊዜ አሁን ከተገኘው ምርት በአሥር እጥፍ እንደምናመርት እንጠራጠርም ብለዋል ።

፬ኛ. ከ፫፻ - ፬፻፺ ሰው በአንድ ጊዜ ለ



ካህናት በልማት ተግባር

ቱ ሊቀ መንበር የሆኑት አቶ ዓለማየሁ ካሣ ናቸው በመጀመሪያ ስለልማቱ እንቅስቃሴ ሲገልጹ ፤

፩ኛ. በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ካህናቱና የሰበካ ጉባኤው አባላት በመተባበር 7000 የባሕር ዛፍ ችግኝ ተክለው ሁሉም ሳይደርቁ ጸድቀዋል በማለት ከተተከሉት የባሕር ዛፎች አንድም የደ

ማስተናገድ የሚችል አዳራሽ አሠርተን አሁን ሕዝበ ክርስቲያኑ እየተጠቀመበት ነው ።

፭ኛ. በቅርብ ጊዜ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ዕቅድ ስላለን ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ኅቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ወደዚሁ ቦታ መጥተው የመሠረቱን



ድንጊያ አስቀምጠውልናል ፤

፮ኛ. የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ የሚሠራበትን ቦታ በሚገባ አስደልድለናል ፤

፯ኛ. የቤተ ክርስቲያኑ ግላን ከመዘጋጀቱም ሌላ ለመሥራት የሚሆን ድንጋይ ሰብስበናል ፤ ሲሚንቶና አሸዋም በመጠኑ አምጥተናል በቅርብ ቀን ሥራው ተጀምሮ ፍጻሜ እንደሚያገኝ ተስፋ እና ደርጋለን ብለዋል ።

፰ኛ. ይኸው የቤተ ክርስቲያኑ አሠሪ ኮሚቴ ቀደም ሲል ወደቤተ ክርስቲያኑ ለሚመጡ ምእመናን የመንገድ ችግር እንዳይገጥማቸው በማሰብ አንድ ድልድይ ከማሠራቱም ሌላ ከአሥፋልቱ መንገድ እስከ ቤተ ክርስቲያኑ የሚያደርሰውን መንገድ በግሬደር አስተካክሎ በመኪናም ሆነ በእግር ምእመናን ያለ ችግር ወደቤተ ክርስቲያኑ እየሄዱ እንዲሳለሙ አድርጓል በማለት አቶ ዓለማየሁ ካሣ የቤተ ክርስቲያኑ አሠሪ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ማብራሪያቸውን አጠቃለዋል ።

ሥራ ጸሎት ነው ጸሎትም ሥራ ነው ተብሎ እንደተነገረው ካህናት በቤተ ክርስቲያን ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር የልማት ተግባርንም ማከናወን እንደሚያስፈልጋቸው ሊያውቁትና ሊረዱት ይገባል ማረስ መቆፈር ተክል መትከል ለካህናት አዲስ ነገር አለመሆኑ ቢታወቅም በከተማ የሚኖሩ አንዳንድ ካህናት የዕረፍት ጊዜያቸውን በከንቱ እንደሚያሳልፉት ስለታወቀ በሚያገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ተግባረ ዕድ እየተቋቋመላቸው በመሥራት ላይ ይገኛሉ ። እንዲሁም ተክል የሚተክሉም እርሻ የሚያርሱም መኖራቸው ታውቋል ።

የዕረፍት ጊዜን በዋዛ በፈዛዛ ከማሳለፍ ይልቅ በሥራ ላይ ማሳለፍ የተቀደሰ ተግባር ነው ከላይ በተጠቀሰው በኩየራ ቅዱስ ገብርኤል ካህናት ከሰበካ ጉባኤውና ከቤተ ክርስቲያን አሠሪ ኮሚቴ ጋር በመተባበር ያከናወኑትን የልማት ተግባር ተመልክተናል ።

# የትንቢትና ምሳሌዎች ትርጉም

አዘጋጅ መ/አ መክብብ አጥናው

፩ኛ - ለማዳ እንስሳት በአምሳል መርገፍነት ሴታዩ አምልኮተ እግዚአብሔርን ሳይዘነጉ ከፈጣሪያቸው ሳይርቁ የኖሩ የቀድሞ አበውና ከነገደ እሕዛብ መካከል የተመረጡና በዘመነ ሐዲስም በክርስትና እምነት የእግዚአብሔር ቤተሰብነትን ያገኙ ምእመናን ምሳሌዎች ናቸው ።

፪ኛ - በስድነት በየበረሃው የሚኖሩ አራዊት ደግሞ ቀደም ሲል ከተፈጥሮ ያገኙትን አምልኮተ እግዚአብሔር ረስተው ዕንጨት ጠርበው ድንጊያ አለዝበው ጣዖት እያመለኩ የሚኖሩ ሕዝቦች ምሳሌ ይሆናሉ ።

፫ኛ - በልብ የሚሳቡ ፤ ተንቀሳቃሽ ፍጥረታትና ክንፍ እያላቸው በአየር ላይ ከፍ ብለው የመብረር ችሎታ የሚያንሳቸው አዕዋፍ ከልባቸው ክፋትና ተንኰል የተነሣ እምነታቸው በእግዚአብ

---

እጅግ በጣም የሚያስደስት ነው በየአብያተ ክርስቲያናቱ አካባቢ የሚከናወነውን የልማት እንቅስቃሴ በጽሑፍ እያዘጋጀን ለአንባብያን የምናቀርበው የልማት ተግባር የጀመሩትን ለማጠናከርና ያልጀመሩት እንዲጀምሩ ለማሳሰብ ነው ።

ለልማት አመች ሆነው በተገኙት አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ ሁሉ የልማት ተግባር ማከናወን የእያንዳንዱ ካህንና ምእመን ተግባር ስለሆነ ሁሉም ሊያስብበት ይገባል ።

ያልታነውትን አብያተ ክርስቲያናት ማሳነፅና ያረጁትን ማሳደስም ከልማቱ አንዱ ክፍል ስለሆነ የኩየራ ቅ. ገብርኤል የቤተ ክርስቲያን አሠሪ ኮሚቴ የጀመረውን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በቶሎ አከናውኖ ለምእመናን መገልገያ ለማትረብ እንዲችል የእግዚአብሔር ፈቃዱ ይሁን እያልን አሳባችንን እናጠናቅቃለን ።

የዜና አቅራቢ ቀ/ልሣነ ወርቅ በዛብህ

ሔር ጸጋ ሳይደግፉ የሥነ ምግባርም ጥራት ሳይኖራቸው በግብዝነት በወላዋይነት የሚኖሩ የስም ክርስቲያኖች ምሳሌዎች ናቸው ።

ታዲያ እኛስ ሦስት ክፍል ሆነው ከተመደቡት ከነዚህ ፍጥረታት ምሳሌነት የትኞችን እንደምንመስል ምርጫችንን እናውቃለንን ? የእምነታችንስ ዕድገት ምን ያህል የተስተካከለ ነው ። በክንፍ እንደሚበሩ አዕዋፍ ጉልማሳነታችን ታድሶ ወደ ክርስቶስ ለመድረስ የምንን ሳፈፍበት የጸጋ ክንፍ አለ ። እርሱም እንደ መርከብ መልሕቅ ሆኖ ነፍሳችን ተደግፋ የምትኖርበት ተስፋ ነው (ዕብ. ፯ ፥ ፲፱) ይህም የማያሳፍር ጽኑ ተስፋ እስካለን ድረስ በእግር ከሚሽከረከሩ በክንፍ ከሚበሩ አዕዋፍ የምንበልጥበት ብዙ መልክም አጋጣሚ አለን ። ይህንም በማስመልከት ነቢዩ ኢሳይያስ "ርግቦች ወደ ማደሪያቸው እንደሚበርሩ ለነዚህ

ከቁጥር ፰፯ - ፰፯ ፦

እግዚአብሔርም አለ "ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እድርገን እንፍጠር" ።

ይህም አባባል ሰው በመልክዓ እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ምሳሌነት ይዞ እንዲገኝ በአርአያ እግዚአብሔር የመፈጠሩ ሁኔታ በይበልጥ ጉልቶ የሚታየው ፦

፩. ሕያዊት ፤ ለባዊትና ነባቢት ነፍስ የተሳለችበት ሆኖ በመገኘቱ ፤

፪. የማሰብ ኃይሉ ከሌሎች በይመነፍስ ሕያዋን ሆነው ከሚኖሩት ፍጥረታት ሁሉ የላቀና የተለየ በመሆኑና ፤

፫. በመልክም የሞራል ዝንባሌው በኩል ነው ።

ይህንም ታላቁ ንጉሥ ሰሎሞን በመጽሐፈ መክብብ ሲገልጥ "አንድ ነገር ብቻ አገኘሁ ፤ ይኸውም እግዚአብሔር ሰዎችን እንደራሱ ቅኖች አድርጎ እንደፈጠራቸው ለማስተዋል መቻል ብቻ ነው ፤



www.ethiopianorthodox.org

እነርሱም ግን ለክፉ ነገር (ለተንኰል የሚጠበቡ ሆነው ተገኙ" ።ይላል (መክ ፯፡፳፱)።

በሌላም አተረጓጐም ዕውነተኞች የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መጋቢዎች የሆኑ መምህራን በራሳቸው አርአያና ምሳሌነት ሰዎችን የመፍጠር ግለትም አስተምረው አሳምነው የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ የማድረግ መብት አላቸው። የዚህንም መብት ዕርግጠኛነት ከሐዋርያው ጳውሎስ አነጋገር መረዳት ይቻላል። እርሱም በ፩ኛ ቆር.፱፡፩ ተጽፎ እንደሚገኝ "ኢኮንኩኑ አግዓዜ ኢኮንኩኑ ሐዋርያ፤ ወኢኮንከሙኑ አንትሙ ግብርየ በእግዚእነ።እኔ ነፃነት ያለኝ ሐዋርያ አይደለሁም እንዴ? እናንተስ በጌታ ፈቃድ የእኔ እጅ ሥራዎች (ፍጥረቶች) አይደላችሁም እንዴ? በማለት ይጠይቃል።

ታዲያ እንግዲህ የጳውሎስ ፈጣሪነት በአምላክነት ደረጃ ሳይሆን የወንጌልን ቃል በመስበክና በማስተማር እርሱን የሚመስሉ፤ የርሱን ፀሠረ ፍኖት (ዱካ) የሚከተሉ አማኞች አዘጋጅቶ ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ መቻሉ ብቻ ነው። እወ መምህራነ ወንጌል የሰውን መንፈሳዊ ሕይወት የመለወጥና እንደገና ሐዲስ ፍጥረት ማድረግ በሚችል በእግዚአብሔር ቃል መዶሻነት በምክርና በተግሣጽ አንፀው ሌሎች ደቀ መዛሙርትን (አማኞችን) በራሳቸው አርአያና ምሳሌ ለመፍጠር መቻል አለባቸው።

በዕርግጥም የጠፉትን ነፍሳት ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ከመቻል የሚበልጥ ጥበብ የለም። ይህም በትንቢተ ዳንኤል ፲፪፡፫፡ "ብዙ ሰዎችን ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘለዓለም ይደምቃሉ" ተብሎ እንደ ተጻፈ መክሮ አስተምሮ የተሳሳቱትን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ራሱ በአምላካዊ ፈቃድ የተደገፈ ሥራ ነው። ስለዚህም በቃሉ አማኚነት እኛም በአርአያችንና በምሳሌያችን ሰዎችን እንፍጠር ብለን ማሰብ ይገባናል።

**የፍጥረት ሁሉ መደምደሚያ**

እግዚአብሔር አምላክ ይህን ግዙፍ ዓለም የሚታየውንም የማይታየውንም ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር ካመጣ በኋላ የፍጥረት ሁሉ መደምደሚያ ጉልላት አድርጎ ያመጣው ሰውን ብቻ ነው።

እዚህም ላይ እግዚአብሔርን እንደ አንድ ሊጋስ ሀብታም ሰው አድርገን መመልከት እንችላለን። ይኸውም በቤቱ ከተጠሩ የክብር እንግዶች በዓይነቱ ተወዳዳሪ የሌለውና በብዛቱም የተትረፈረፈ ታላቅ ግብዣ የሚያዘጋጅ አስተዋይ እንግዳ ተቀባይ የሆነ ሊጋስ ሰው ምግብና መጠጡን በየዓይነቱ ለማቅረብ ብቃት ግብዣ መሰናዶቱን ከማረጋገጡ በፊት እንግዶችን አይጠራም።

ከሁሉም በተቀዳሚ ግብዣ በሚደረግበት አዳራሽ ለእንግዶቹ በቂ ቦታ መኖሩን፤ ወንበር፤ ጠረጴዛው በትክክል ተደርድሮ ማሆኑ፤ ኩባያው፤ ዋንጫና ጥዋው ባጠቃላይም ለምግብና መጠጥ ማቅረቢያ የሚያስፈልጉት ነገሮች ሁሉ መሟላታቸውን በጥንቃቄ ይመረምራል። ይህንም ሁሉ ካረጋገጠ በኋላ ሆደ ሰፊ ነገር አላፊ የሆኑ አስተናባሪዎችን መርጦ ያቆማል፤ ከዚያም ቀጥሎ የክብር እንግዶቹን በብሩህ ፈገግታ እየተቀበለ ወደግብዣው አዳራሽ መምራት ይጀምራል።

ልክ በዚሁ ዓይነት ሁኔታ እግዚአብሔር አምላክም ይህን አስደናቂ ዓለም ከፈጠረ በኋላ የሰው ዘር ሁሉ ለምግብና መጠጥ፤ ለልብስና ለመጠለያ የሚጠቀምባቸውን ነገሮች ሁሉ በማትረፍረፍ አብዝቶ የማዘጋጀቱን ተግባር በቅድሚያ አከናወነ። ከዚያም ሁሉ በኋላ ሰውን በመልኩና በምሳሌው ፈጥሮ እጅግ ውብ የሆነ ይህን ዓለመ ተድላ እንዲደሰትበት ጋበዘው ( )።
ቅዱሳን መላእክትንም የርሱ አስተናባሪዎች ሆነው ያገለግሉት ዘንድ ፈቀደ.

ሆኖም እግዚአብሔር ከታላቅ ግብዣ አዘጋጆች ሁሉ በላይ ነው። ሰውም ከተፈጥሮው ታላቅነት አንፃር ሲታይ ለክብር እንግድነት ከሚጠሩ ተጋባዦች ሁሉ የላቀ ቤተሰብነት አለው። እግዚአብሔር ሰውን ለመላው ዓለም መጋቢና ገዢ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ አድርጎ ሾሞታል።

ታዲያ ይህ ሁሉ መልካም ነገር በተደረገለት ፈንታ ሰውስ ለፈጣሪው ለእግዚአብሔር የነበረው ታማኝነት ምን ያህል የተጠበቀ ነበር ፈጣሪውስ የጣለበትን አደራ ለመጠበቅና ኃላፊነቱን በፍጹም ታማኝነት ለመወጣት የተዘጋጀ ነበርን የነዚህን ጥያቄዎች በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 እንመለከታለን።

## "የቅኔ አዝመራ ይሰብሰብ በወቅቱ"

በወሎ፤በጐጃም፤በትግራይ፤በጐንደር
ተጉዞ ለማጥናት የቅኔን ምርምር፤
በየአድባራቱ ያለዕረፍት በመዞር
ሊቆች ያካባቱት የግሥ ምርጥ ዘር
የአገባብ ሙያ፤የግሥ ዕርባ ትምር
የሰምና የወርቅ ፤ ጥልቅ ፤ ረቂቅ
ምሥጢር፤
የምርምር ውጤት የቅኔ ቅንብር
እንደተበታተነ በከንቱ እንዳይቀር
የቅኔ አዝመራ በወቅቱ ይመኸር
ፈሩን አስስልሶ ተልሞ ባዘጋጀው
ሁዳድ ጉባዔ ላይ፤መምሕሩ የዘራው
ወቅቱን በመጠበቅ ሳይቆይ የበቀለው
የዘሩ ተተኪ የቅኔ ቡቃያው
ታርሞ እያደገ አብቦ የታየው
ዘርዝሮ አሽቶ ፍሬው የጐመራው
ምሑሩ አገዳ፤ፍሬ ተሸካሚው
ከላይ ፍሬው ከብዶት ሲታጠፍ
ከአንጓው
ፍሬውን የሚለቅም ሰብሳቢ ካላየው
ከአፈር ላይ በቅሎ፤በጥዋት የቆየው
ኋላ ተመልሶ አፈር እንዳይበላው
እንኳን ታጭዶ፤ታሥሮ ተከምሮ
ነዶው
ፍሬውን እያየ በወቅቱ ለቃረመው
ችግር የሚያስወግድ የተረሳ ቀድሚያው
የቅኔ አዝመራ ሰብሳቢ ይኑረው።
በኦርቶዶክሳዊት ቅድስት አቅሌስያ፤
በቅኔ አብቃይዋ ምድረ ኢትዮጵያ
ባግባቡ እንዲስፋፋ የቅኔ ምርት ሙያ፤
ቅኔን የሚያበቅል ሁዳድ (ጉባዔ) ኒቅያ
ማዕድ ተሚጦ ሳያጣ ቡቃያ
ከሊቃውንት ሀብት የዓለም ገበያ
ለቅኔ አምራቾች ይቅረብ ማዳበሪያ።
በምርምርና የፍልሰፋ ሥራ
በአዕምሮ ግኝት የምሥጢር ፈጠራ
ማግኘት የፈለገ የቅኔን ቆጠራ
ሊሸምት ሲመጣ፤ከሩቅ ዞሮ ጋራ
እጥቶ እንዳይመለስ ችግር እያወራ
የዘር ማከማቻ ተሥርቶ ጐተራ
ይሰብሰብ በወቅቱ የቅኔው አዝመራ
መርሐ ጽድቅ ገ/ግርያም

# ዐቢይ ጾም

# እንደ ክርስትና እምነታችን

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ምንም እንኳ የሰው ልጅ በደለኛ ቢሆንም ሰዎች ንስሐ ገብተው በጾምና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ከተመለሱ እግዚአብሔር የሰዎችን ሁሉ በደል ይቅር ያላለበትና ችግራቸውንም ሁሉ ያላቀለለበት ጊዜ እንደሌለ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። ስለሆነም ሰዎች ኀጢአታቸውን አስወግደው ከፈጣሪያቸው ጋር ተገናኝተው ምድራዊና ሰማያዊ ጸጋ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚቀበሉበት በጾምና በጸሎት ነው።

በመሠረቱ ጾም ሲባል እንደ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለተወሰኑ ጊዜያት እህልና ውኃን ከመቅመስ መቆጠብ ብቻ ሳይሆን ከቂምና ከበቀል በጠቅላላም ከክፉ ነገርን ሁሉ ከማድረግ ለመጨረሻ ጊዜ ትቶ በየጊዜያቱ ቁጥር ያለልክ ከመብላትና ከመጠጣት ተቆጥቦ ሁሉንም ነገር ፈጥሮ ለሚገዛ እግዚአብሔር ራስን ማስገዛት ነው።

ቀደም ሲል በአለፉት ዘመናት የነበሩት አባቶች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ለመረዳት ቅዱሳት መጻሕፍትን መለስ ብለን ስንመረምር በሌላ መንገድ ሳይሆን በጾምና በጸሎት እንዲሁም በጐ ነገርን ሁሉ በማድረጋቸው እንደነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ያሥረዱናል። ለምሳሌ .... ዘፀ ፴፬ ፳፰ ፫ኛ ነገ ፲፱.፩-፳፫ ፩ኛ ሳሙ. ፩.፩-፲፪ ዳን. ፲.፩-፲ ። የመሳሰሉትን ሁሉ ብንመለከት ብዙ ቅዱሳን አባቶች በጾማቸውና በጸሎታቸው ከእግዚአብሔር ጋር እንደተገናኙና እንደተነጋገሩ ችግራቸውም ሁሉ እንደተቃለለላቸው መረዳት እንችላለን በተለይም ዘጸአ ፴፬.፳፰ ውስጥ ያለውን ስናነብ በዚያ ዘመን እስራኤልን ይመራ የነበረው ሙሴ ለሰዎች ሁሉ መመሪያ የሚሆን ሕገ ኦሪትን (አስሩ ትዕዛዛትን) ለመቀበልና ከእግዚአብሔርም ጋር ተገናኝቶ ቃል በቃል ለመነጋገር የቻለው በሲና ተራራ ላይ ሱባዔ ገብቶ በጾምና በጸሎት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እህልና ውኃን ሳይቀምስ በመቆየቱ እንደነበር ለመረዳት እንችላለን።

በሌላ በኩልም ደግሞ ነቢዩ ዳንኤል እንደ ሌሎች ቅዱሳን አባቶች ከፈጣሪው እግዚአብሔር ጋር ለመነጋገርና ጸጋም ለማግኘት ሲል በጾምና በጸሎት ተወስና ሱባዔ ገብቶ በነበረ ጊዜ በጾም ወራት መበላት ከማይገባቸው ምግቦች ሁሉ ተቆጥቦ እንደነበር ሲገልጽ "እኔ ዳንኤል ሶስት ሳምንታት እስኪፈጸሙ ድረስ ዘይት አልተቀባሁም"(ዳን. ፲.፪-፫ ።)

በማለት ነቢዩ በጾመባቸው ሳምንታት ሁሉ በጾም ጊዜ ለምግብነት መቅረብና መበላት ከማይገባቸው የምግብ ዓይነቶች ሁሉ እንዳልተመገበ ገልጾ በጾመባቸው ሳምንታት ሁሉ በንፁህ ልቡና ከማንኛውም መጥፎ ነገር ሁሉ ርቆ በጾምና በጸሎት ፈጣሪውን በመለመኑ የእግዚአብሔር ክብር እንደተገለጸለት ከምዕ.፲.ቁ.፳-፱ ባለው ውስጥ ገልጿል።

እንዲሁም ደግሞ በሌላ መልክ ሌሎችም እንደ ዳንኤል ቀደም ብለው የነበሩት አባቶች ሁሉ ልዩ ልዩ ሥራዎቻቸውን ሁሉ ከመጀመራቸው በፊት ሥራዎቻቸው የተቃኑ እንዲሆኑላቸው እግዚአብሔር አምላካቸውን በጸሎት ይጠይቁ ነበር ፩ኛ ነገ ፫.፬-፲ እንዲሁም ከበድ ያለ ችግር በደረሰባቸውም ጊዜ በጾምና በጸሎት ተጸምደው የደረሰባቸው ችግር ሁሉ እንዲወገድላቸው ፈጣሪያቸውን ሲለምኑ እግዚአብሔር ሐሳባቸውን ሁሉ ተቀብሎ የደረሰባቸውን ችግር ሁሉ ያቃልል ነበር።

ዓለምና በዓለም ላይ ያሉት ነገሮች ሁሉ ሕልውና ከማግኘታቸው በፊት የነበረው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ለማዳን ሲል የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥጋ ለብሶ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ ሰዎችን የማዳን ሥራውን ሁሉ በጾም ጀመረ(ማቴ. ፬.፲፬)ዕለቱን በገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ በጾሙም ወራት እንዲፈትነው ሰይጣን በቀረበ ጊዜ ሰይጣንን ድል አድርጓል።

ለሰዎች ለበጐ አድራጐታቸው ሁሉ መሰናክል የሆነው ሰይጣንን "ሐር እምድህሬየ ሰይጣን" በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጨረሻ ጊዜ የሰይጣንን ኃይል ሰብሮ አባርታል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጾሙም ለእኛ ሁሉ አርአያ ሁኖ አጋንንትን በጾሙ አባርአል ስለ ሆነም በየጊዜው በጾምና በጸሎት አጋንንትን ሁሉ እንድናባርር ጌታ ኢየሱስ "ይህን ጋኔን ከጾምና ከጸሎት በስተቀር የሚያስወጣው የለም" በማለት ጾምና ጸሎት የአጋንንት ሁሉ ድል ማድረጊያ የእግዚአብሔርና የሰዎች መገናኛ መሆኑን በማይታበለው አምላካዊ ቃሉ አስረድቷል።

ስለዚህ በጌታችን ቃል መሰረት በየጊዜው ለጾምና ለጸሎት መዘጋጀት ያስፈልገናል በጾማችንም ጊዜ ሁሉ የምንጾመውና የምንጸልየው ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለሀገራችን ለወገናችን ሁሉ መ


www.ethiopianorthodox.org

# የደረሞ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ተፈጽሞ ታቦቱ ገባ ዘግይቶ የደረሰን ዜና

ደረሞ ደብረ ምሕረት ቅ. ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው በጎንደር ሀ/ስብከት በደብረ ታቦር አውራጃ በፋርጣ ወረዳ ነው ፤ በዚያው አካባቢ ጥንታውያን ተብለው ከሚጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ነው ፤

የተመሠረተው በዳግማዊ ዓፄ ዳዊት ሲሆን ከ፭፻ ዘመን በላይ ሆኖታል ። ይኸው ቤተ ክርስቲያን ከዘመን ብዛት የተነሣ በማርጀቱ እንደ ጌት ማደስ እንደሚቻል በደብሩ የሚኖሩ ምእመናንና አዲስ አበባ የሚኖሩ የዚሁ ደብር ተወላጆች ስለ ጉዳዩ ለሚመለከተው የበላይ አካል ጥያቄ እያቀረቡ ጉዳዩ ሳይሳካላቸው ቆይተው ነበር ፤

የሰበካው ምእመናን መጋቢት ፲ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ.ም ተሰብስበው በመወያየት ኑዋሪነታቸው አዲስ አበባ ከተማ ሆኖ የኢትዮጵያ ተሽከርካሪ መኪናዎች አገልግሎት ድርጅት አንበሳ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ሹፌር የሆኑትን አቶ መለሰ አስረስን የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ አስፈጻሚ አድርጎ መረጣቸው አ... መለሰም የምእመናኑን ምርጫ ተቀብለው ርዳታ እንዲጠይቁላቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ደብዳቤ የጻፉት የዚሁ ደብር ተወላጅ ለሆኑትና ምዕራብ ጀርመን ለሚገኙት ዶ/መርዓዊ ተበጀ ነበር እርሳቸውም ከበጎ አድራጊዎች ክርስቲያኖች በመጠየቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ብር 8000 ልከውላቸዋል በተጨማሪም መጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ.ም ከእንዚያው በጎ አድራጊዎች ምዕራብ ጀርመን ከሚገኙት ክርስቲያኖች በኢትዮጵያ ብር ፳፪.ሺ. ፩፻፲፬ ፳፪ ተልኮላቸው ከጎንደር ሀ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ መርቆሬዎስ እጅ ተረክበው ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ማስፈጸሚያ እንዲውል አድርገዋል ፤

በእግዚአብሔር ቸርነት በምዕመናን ኅብረትና አስተዋጽኦ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ተፈጽሞ ግንቦት ፲፪ ቀን ፸፰ ዓ.ም ታቦቱ አዲስ ወደተሠራው ቤተ ክርስቲያን ገብቷል በበዓሉም ላይ በአካባቢው የሚኖሩ የአድባራትና የገዳማት አስተዳዳሪዎች ሊቃውንት በሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን ተገኝተዋል ሲል ዜናው አስረድቷል ዜናው ማብራሪያውን በመቀጠል ማንም ሰው ተወልዶ ያደገበትን ደብር እንደወላጅ ይናፍቃል አቶ መለሰ አስረስ ግን ስለ ደረሞ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ያላቸው ፍቅር ከሁሉም የላቀ ነው ብሏል ፤

ዜናው በተጨማሪ አቶ መለሰ አስረስ ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ይህንን ያህል ጥረት ሲያደርጉ ለግል መኖሪያ ቤታቸው የቤተ ክርስቲያኑን ያህል ጥረት እንዳላደረጉ ገልጸው የቅዱስ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ሥራ ከመኖሪያ ቤታቸው አስበልጠው የሚመለከቱትና ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን ሳይቆጥቡ ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ስላዋሉ እጅግ በጣም ሊመሰገኑ የሚገባቸው ምእመን መሆናቸውን አስረድቷል ።

በሕይወት እያለን በሠራነው በጐ ሥራ ይህችን ምድራዊት ዓለም በሞት ከተለየናት በኋላ አንደኛ የማታልፈውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ወርሰን ለዘለዓለም በተድላ ነፍስ እንኖራለን ሁለተኛ ስማችን ከምድር በላይ በተተኪው ትውልድ ሲጠራ ይኖራልና ሁላችንም የአቶ መለሰ አስረስንና የሌሎችንም በጎ አድራጊዎች አርአያ በመከተል የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት ብንሠራ የድካማችን ፍሬ ከቸሩ ፈጣሪያችን ለማግኘት እንችላለን በማለት ዜናው አሳቡን አጠቃሏል ።

አቅራቢ መርሐ ጽድቅ ገ ማርያም

---

...ን መረዳት አለብን ይህን በማስመል... ነቢዩ ሳሙኤል ለሰዎች አለመጸለይ እግዚአብሔርን መበደል መሆኑን ሲገልፅ "ስለእናንተ መጸለዩን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ (፩ኛ ሳሙ. ፲፪.፳፫) በማለት እንደገለጸው ለሰዎች ሁሉ በ... ነገር እንዲገጥማቸውና ለሀገራችንና ለዓለም ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰላም እንዲበዛ በነቢዩ ሳሙኤል ትእዛዝ መሰረት በጸሎታችን ጊዜ ሁሉም ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋና በረከት እንዲያገኙ መጸለይ አለብን ።

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

# ስብከተ ወንጌል ክፍል አራት

ወንጌልን ለመስበክ ከሁሉ አስቀድሞ የራስ ፍላጎትና ፈቃደኝነት የእግዚአብሔርም ጥሪ ያስፈልጋል በጾምና በጸሎትም እራስን አዘጋጅቶ ከመንፈስ ቅዱስ የህይወት መንፈስ መቀበል ያሻል ይህንንም ከክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ለመረዳት ይቻላል ። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፳ ቁጥር ፲፱-፳፫ እንደሚከተለው ይነበባል "አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ ። ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ። ኃጢአታቸውም ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል ያያዛችሁባቸውም ተይዞባቸዋል ። አላቸው" ይህም የሚያመለክተው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለም ኃጢአት ተሰቅሎና ሙቶ ከተነሳ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን በየሐገሩ እንደላካቸውና በዚህም ጊዜ ወንጌል መስበክ እንደተጀመረ ነው ወንጌሉንም እንዲሰብኩና የምስራቹንም እንዲያወጁ ወደ ዓለም የተላኩት ሐዋርያት የእግዚአብሔር ጥሪና የመንፈስ ቅዱ... ኃይል ... ብቻ ሳይሆን በራሳቸውም ፍላጐትና ፈቃድ መልዕክቱን ለማዳረስ ወደፊት የሚገጥማቸውን መከራ እንደማይፈሩ ያስገነዝበናል ። ምክንያቱም ክርስቶስ መከራ ችግር እንደሚገጥማቸው ስለሚያውቅ የራሱን አሸናፊ መንፈስ እፍ ብሎባቸው ነበርና ነው ይህም አሸናፊ መንፈስ ለደቀመዛሙርቱ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው በፈቃደኝነትና በፍላጎት ወንጌልን ለመስበክ ለሚነሱ የወንጌል መምህራን ሁሉ የሚሰጥ ኃይል ነው ።

ደቀመዛሙርቱም በዚህ አኳኋን ወንጌልን እየሰበኩ ስሙን የማያውቁትን አህዛብን ስሙን መጥራት የማይችሉትን እንደበቶችን እንዲያመልኩትና እንዲጠሩት ከማድረጋቸውም በላይ ቤተ ክርስቲያንም እድገት አግኝታና ተስፋፍታ የክርስቶስን ፍቅር እንድትሰብክ የወንጌል ሰረገላ እንድትሆን አድርገዋታል ።

ይህ ከሆነ በአክሱም ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ ስብከተ ወንጌል ይዞታና ሂደት እንዴት ነበር የሚለውን በዛሬ ጽሑፋችን እናቀርባለን ይህንንም ለማወቅ ቢፈለግ የዘመኑ ታሪክ እንደሚያብራራው በስድስተኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ የነበረው የአክሱም መንግሥት በሁሉ ነገር የበረታና የታፈረ ፤ በጣም የተስፋፋና የቀይ ባህርን ዙሪያ ለመቆጣጠር ኃይል ያለው ሲሆን እስከ የመን ድረስ ዘምቶ ለተጠቁት በዛ የሆነ ኃይለኛ መንግሥት ነበረ ። ይኸውም ሰላማውያን ሰዎች የነበሩትን ሰማዕታተ ናግራንን የሞት ጽዋ ያጠጡአቸውን ግፈኞች መልሶ ያንኑ የሞት ጽዋ አጠጥቶ እንደተበቀላቸው በየዓመቱ ህዳር ፳፮ ቀን የሚነበበውን መጽሐፈ ስንክሳር ማንበብ ያስፈልጋል ይህም በመሆኑ ቤተ ክርስቲያኗ ከአገሪቱ ጋር አብራ ስለአለች መንፈሳዊ ኃይልም ስላገኘች ከቁስጥንጥንያና ከአንጾኪያ ፤ ከኢየሩሳሌምና ከኮብት አብያተ ክርስቲያናት ጋር በየጊዜው ግንኙነት ታደርግ ነበር ። አማኞችም ሆኑ ልኡካኑ እየሄዱ የመጎብኘትና እየሄዱ ጉዳያቸውን ፈጽመው የመመለስ ዕድል ነበራቸው ስለዚህም የተነሳ ስብከተ ወንጌል በሁሉም ዘንድ ተስፋፍቶ ነበር ። በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ዋና መዲናየነበረችው የአክሱም ከተማ ዋናው የስብከተ ወንጌል ማዕከል ስትሆን አያሌ አህጉረ ስብከቶች ነበሩ ።

አህጉረ ስብከቶች ሊበዙ የቻሉት የክርስትና ሃይማኖትን ቤተ ክርስቲያን እንዲስፋፋ ስላደረገች ስብከተ ወንጌል ከፍ ያለ ዕድገት አግኝቶ ነበር ። ይህም ሊሆን የቻለው በዚያን ዘመን ከነበሩት ክፍለ ሀገሮች ሁሉ የወንጌል መምህራን እየተላኩ ትምህርት ያደርሱ ስለነበር ነው ይኸውም አክሱም የኢትዮጵያ መዲና በነበረችበት ጊዜ እስከ እርስዋ ብዙ አህጉረ ስብከቶች እንደነበሩ ታሪክ ያስረዳል ።

ስለ ጥንታውያን አህጉረ ስብከቶችም በውጭ ታሪክ እንደሚገለጸውም በየዘመኑ ስማቸው በመለዋወጡ ሳይሆን አይቀርም ከእነዚህም ስማቸው የሚታወቁትን እንገልጻለን አንደኛ ባህረ ነጋሽ (ባህረ ምድር) ሁለተኛ አዶሊስ ሦስተኛ ዘይላ አራተኛ ገላቲ (የጂ) አምስተኛ መርዌ ስድስተኛ ...ደረቤ ሰባት እንኮበር ስምንተኛ ማጂ ዘጠነኛ ባሌ አሥር ፋና (ዛሬ የየመን ዋና ከተማ የሆኑ የታወቁት እነዚህ ሲሆኑ የተረፉትን ግን ስማቸው ባለመታወቁ ልናቀርባቸው አልቻልንም እነዚህ ሁሉ የስብከተ ወንጌል ማህበር ተቋቁሞባቸው የወንጌል መምህራን ተመድበውላቸው ወንጌል የሚሰበክባቸውና ብዙ ምዕመናን እየተሰበሰቡ ተምህርተ ወንጌል የሚማሩባቸው ቦታዎች ነበሩ ።

በነዚህም የመሰብሰቢያ ቦታዎች ወንጌልን የሚያስተምሩ መምህራንም ሆኑ ትምህርቱን በሚያዳምጡ አማኞች ዘንድ ፍቅርና መግባባት የእርስ በእርስ መዋደድ በመካከላቸው ይታይ ስለነበር በምሳሌነታቸው ብዙ አማኞችን ይስቡ እንደነበር ታሪክ ይናገራል ። መምህራንም የሚያስተምሩት ምዕመናን ሊያውቁ የሚገባውን እንዲያውቁ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ነገር ሁሉ እየሠሩ በእምነትና በምግባር በየጊዜው ከፍ ከፍ እንዲሉ በዓይናቸው የሚያዩዋቸውን በልባቸው የሚያስቡዋቸውን ክፉ ነገሮች ሁሉ ጠልተው ለራሳቸው ሊያደርጉላቸው የሚወዱትን ለሌሎች እንዲያደርጉ ያስተምሩዋቸው ነበር ። ይህም በመሆኑ ምዕመናኑ ብዙ የመንፈስ ፍሬ ሊያፈሩ በመቻላቸው ስብከተ ወንጌል ታላቅ ዕድገት እንዳገኘ ይኸው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያብራራል ይህም የመንፈስ ፍሬ የተገኘው የወንጌል መምህራን የምዕመናን ሕይወት የወይን ግንድ ከሆነው ከክርስቶስ ጋር እንዲያያዝ በማድረጋቸው ነው ስለዚህም የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፭ ከቁ. ፩-፭ የሚከተለውን ያስተምረናል "እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እኖራለሁ ብዙ ፍሬም ያፈራል ብሏል ።

ይህንንም አባባል ልናስተውለው ይገባል ቅርንጫፎቹ ከወይኑ ሥርና ግንድ የሚመጣውን ማንኛውንም ምግብ እየተመገቡና የሚወርደውንም ጠል ጠጥተው አድገው ብዙ ፍሬ እንደሚያፈሩ ሁሉ እኛም ህይወት የምናገኘውና ብዙ የመንፈስ ፍሬ የምናፈራው በወንጌል ትምህርት ተከትትለን አድገን ህይወታችንን ከክርስቶስ ጋር አንድ ያደረግነው እንደሆነ ነው የወንጌልንም ትምህርት ሳንሰጥ ካደግንና ሕይወታችንም ከክርስቶስም ከተለየ ግን ህይወት የለንም በእርሱ ከኖርንም መልካምፍሬ እናፈራለን ። ከእርሱ ጋር አንድነት እንዲኖረን የሚረዳን ያልተማሩትን ስናስተምር የታመሙትን ስንጎበኝ የተቸገሩትን ስንረዳ በጠቅላላው እርስ በእርሳችን ስንፋቀርና መልካም ሥራ የሰራን እንደሆነ ነው ለምሳሌ ስርና ግንድ ቅርንጫፍ ቀንበጥና ቅጠል አበባና ፍሬ እነዚህ ሁሉ የማይለያዩ የማይከፋፈሉ የሚያጋሩ አንድ ህይወት ያላቸው ከአንድ ዛፍ የሚገኙ ናቸው እነዚህ ሁሉ



www.ethiopianorthodox.org

# "ከእንግዲህ የኃጢአት ዕዳ የለብንም"

"በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽፈት ደመሰሰው እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል"

የሰው ልጅ በምድራዊ ኑሮው ብዙ የሚጨነቅባቸውና የሚያስብባቸው ነገሮች አሉ ። አንድ ዘመናዊ ቤት ሠርቶ መኪና ገዝቶ ከሌሎቹ በልጦ ደስተኛ ሆኖ ለመኖር ይጨነቃል ታማኝነቱን ክዶ የራሱ ያልሆነውን ንብረት ያባክናል ለግል ጥቅሙ ያውላል በዚህ ሁሉ የበለጠ የመንፈስ ጭንቀት ይደርስበታል ። በመጨረሻም በጭንቀት ዓለም ውስጥ እንዳለ እራሱ ባመጣው መጥፎ ዕዳ ውርደትና ጉስቁልና ይገጥመዋል። ሌላው ደግሞ የዕለት ኑሮው አልሳካለት እያለ ወጥቶ ወርዶ ነግዶ አትርፎ ለዕለት ጉርስ ለዓመት ልብስ ለማግኘት ከሌላው በአራጣ ወይም በወለድ ገንዘብ ይበደራል በጠቅላላው የሰው ልጅ በልዩ ልዩ መንገድ ለልዩ ልዩ ተግባር ከግለሰቦች ገንዘብ ይበደራል በመጨረሻ የሚከፍለው ወይም የሚከፍልለት ሲያጣ በዕዳ ይያዛል ወይም የዕዳ ባለቤት ይሆናል ያለው ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረቱ በሆነ በአልሆነው ተሸጦ ያልቃል በእርሱም ላይ የእሥራት ፍርድ ይፈረድበታል ። አንዳንድ ጊዜም ያለበትን ዕዳ መለስ ብሎ ሲያስበው መንፈሱ ይታወክበታል የአእምሮ ዕረፍት ያጣል ብዙ ውጣ ውረድ ይደርስበታል ራሱን በራሱ ወደሚያጠፋበት ደረጃ ይደርሳል ።

የሰው ልጅ ይህ ሁሉ የኑሮ ምስቅልቅል ኑሮ ውኻንብር የሚደርስበት በዚህ ዓለም ደስተኛ ሆኖ ለመኖር በሚያደርገው የኑሮ ትግል ውስጥ ነው ። በዚህ ሁሉ መከበርና መዋረድ ፡ ማጣትና ማግኘት መሾምና መሻር ፡ መደሰትና ሐዘን ይፈራረቁበታል አንዳንድ ጊዜ በዚህ ሁሉ ቁሞ የሚከራከርለትን ወገን ሲያገኝ በሌለ ጊዜ ደግሞ ፈጽሞ ጠያቂ ያጣል ። ይህ ሁሉ የግል ፍላጐቱን ለማርካት ሲል ያመጣው የዕዳ ውጤት ነው ። የሰው ልጅ ይኸን ሁሉ የዕዳ መዘዝ በሚያመጣበት እንቆቅልሽ ዓለም ውስጥ የኃጢአት ዕዳስ የለበትምን የኃጢአት ዕዳስ የሚደርስበት የግል ምኞቱንና ፍላጐቱን ለማርካት በሚያደርገው የኑሮ ትንቅንቅ ጊዜ አይደለም ? ለምሳሌ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች የኃጢአት ዕዳ የመጣባቸው የበላይ ሆኖ ለመኖር ሲሉ በራሳቸው ምኞት ተስበው የአምላካቸውን ትእዛዝ በተላለፉ ጊዜ መሆኑን ማንም ማን አይዘነጋውም ማንኛውም የሰው ልጅ አዳማዊ ጠባይ ስለአለው በራሱ ምኞት ተማርኮ ከኃጢአት ዕዳ ውስጥ ይዘፈቃል የኃጢአት ዕዳ ስለአለበትም ዘለዓለማዊ ሞት ተፈርዶበታል ።

ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ "ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአት ስለአረጉ ሞት ለሰው ሁሉ የደረሰ ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበርና ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቆጠርም ፣ ነበር ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩ ላይ እንኳ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ" ሲል ያስረዳል ። ሮሜ ፭፡ ፲፪ - ፲፬

የሰው ልጅ አዳማዊ ጠባይ ስለአለው በኃጢአት ዕዳ ተይዞ ይሠቃይ እንደነበር በዚህ መልእክት ለመረዳት ይቻላል ። ከዚህ ከኃጢአት ዕዳ ነፃ የሆነውም ለመሆን የምንከተለውም በክርስቶስ ሞት ነው ። ክርስቶስ ከፍጥረቱ ሁሉ አብልጦ ስለሚወደን የኃጢአት ዕዳችንን በመስቀል ላይ ከፍሎልናል ። ወደፊትም በክርስቶስ ከአመን የኃጢአት ዕዳ አይኖርብንም ። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ"በእኛ ላይ የነበረውንና የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽፈት ደመሰሰው እርሱንም ከመስቀል ላይ ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል" ሲል ያስረዳል ።

እንግዲህ እያንዳንዱ ሰው በክርስቶስ ሞት ከኃጢአት ዕዳ ነፃ ከሆነ በኋላ ተመልሶ በኃጢአት ዕዳ ተይዞ ዘለዓለማዊ ጭንቀት እንዳይደርስበት መጠንቀቅ ይኖርበታል የገንዘብ ዕዳ ያለበት ሰው ስለ ዕዳው ብዙ ያስባል ይጨነቃል ዕዳውንም የሚያቃልልለት ወገን ቢያገኝ ይመኛል ከጭንቀት የተነሣም ሕይወቱን እስከማጣት ይደርሳል ። የኃጢአት ዕዳ ያለበት ሰው ከዚህ የበለጠ ጭንቀትና የመንፈስ መረበሽ ይደርስበታል ። ስለሆነም ከኃጢአት ዕዳ ነፃ ለመሆን የሚችለው ራሱን ዝቅ ዝቅ አድርጎ በሰዎች መካከል ተገኝቶ ስለሰዎች ኃጢአት ተላልፎ በሞተው በክርስቶስ ያመነ እንደሆነ ነው ያለክርስቶስ እምነት የሰዎች የኃጢአት የዕዳ ደብዳቤ ሊሰረዝ አይችልም ።

ከዛፉ ጋር አንድ ሆነው ሲሰሩ ብዙፍሬ ሊያፈሩ ስለሚችሉ ሁሉም ይጠቀምባቸዋል እኛም ህይወታችንን ከክርስቶስ ጋር አንድ አድርገን ከሠራን በሥራችን ብዙ ሰዎችን ልንጠቅም እንችላለን አገልግሎታችንም ለሁሉ ሊደርስ ይችላል በእርሱ አምነን ተዘጋጅተን ወንጌልን የሰበክን እንደሆነ ቤተ ክርስቲያን ዕድገትን ታገኛለች ስብከተ ወንጌልም ይስፋፋል ምዕመናንም ከቀን ወደ ቀን እየበረከቱ ይሄዳሉ አጥፊዎችም ከክፋት ወደ በጎነት ከጭቅጭቅ ወደ ሰላም ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ይመለሳሉ ። በጠቅላላው በሰዎች መካከል ሰላም ይሰፍናል

እንግዲህ በስብከተ ወንጌል የተመደብን በልዩ ልዩ የሥራ መስመርም እንድንሠራ የተሰማራን ሁሉ በሞያችንና በችሎታችን ሠርተን ለሀገርና ለቤተክርስቲያን መልካም የሥራ ፍሬ እናፍራ ሥራችን ከፍሬአችን ይታወቃልና ።

ይቀጥላል

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



አትሳቱ ሴሰኞች ፣ ቢሆኑ ወይም ግብረ ሰዶም የሚሠሩ ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካራሞች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም " ካለ በኋላ "ከእናንተ እንዳንዶቹ እንደዚህ ነበራችሁ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል ተቀድሳችኋል ጸድቃችኋል" ሲል ያስረዳል ፩ኛ ቆሮ. ፮፡፱-፲፪

ሰዎች ሁሉ ሊከፍሉት በማይችሉት በኃጢአት ዕዳ ተይዘው ኃጢአት በአመጣው በሞት እንቅልፍ ተውጠው በሚጨነቁበት ጊዜ አምላካችን ክርስቶስ በቅዱስ መስቀሉ ላይ የኃጢአት ዕዳቸውን አስወግዶላቸዋል ። ስለዚህ ሁላችንም በስሙ ተቀድሰናል በስሙ ከብረናል በስሙ ጸድቀናል ስለኃጢአታችን በሞተልን በክርስቶስ ከአመን ሁለተኛ በኃጢአት ዕዳ ልንያዝ አንችልም ከእርሱ ጋር በሕይወት ለመኖር በትንሣኤው በክብር እንነሣለን ። ስለዚህ ክርስቶስ በሞቱ የዕዳ ደብዳቤያችንን ከሰረዘልን በትንሣኤው ከእርሱ ጋር ከአስተነሣን በእግዚአብሔር ሕያው ነን እንጂ ሙታን እንዳይደለን መገንዘብ ይኖርብናል ። እንደአለፈው በሰውነታችን ኃጢአት እንዳይሰለጥንብን ኃጢአት እንዳይገዛን የራሳችን ምኞት ታዛዦች እንዳንሆን በእምነት ወደ እግዚአብሔር ልንቀርብ ይገባናል ። ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ "እንግዲህ ለምኞት እንዳትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ ብልቶቻችሁን የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ ። ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ " ኃጢአት አይገዛችሁምና ፣ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁም ። " ሲል ያስረዳል ። ሮሜ ፮.፲፪-፲፬

በኃጢአት ዕዳ ተይዘን ከእግዚአብሔር አንድነት ተገዘን ከኖርን በኋላ በሞት የኃጢአት ዕዳችንን በከፈለልን በክርስቶስ ወደ ባሕርይ አባቱ ወደ እግዚአብሔር አብ ወደ ባሕርይ ሕይወቱ ወደ መንፈስ ቅዱስ ቀርበናል ማህደረ ሥላሴ ሆንናል ወደ ራሱና ወደ ባሕርይ አባቱ ወደ እግዚአብሔር ወደ ባሕርይ ሕይወቱ ወደ መንፈስ ቅዱስ ከአቀረበን ማህደረ ሥላሴ ከአደረገን በኋላ ዳግመኛ በኃጢአት ዕዳ ተይዘን እንዳንጨነቅ ከእንግዲህ መጠንቀቅ ይገባናል ። ብዙ የገንዘብ ዕዳ ያለበት ሰው ዕዳውን ለመክፈል ከአለመቻሉ የተነሣ ተከሶ ለፍርድ እንደሚቀርብ ስለሚያውቅ ብዙ ይጨነቃል የሕሊና ዕረፍት ያጣል መኖሩንም ከሙታን ጋር እንደ ሙታን ከሚቆጥርበት ደረጃ ይደርሳል ። እንደዚሁም የኃጢአት ዕዳ ያለበት ሰው ቢወድም ባይወድም አንድ ቀን በኃጢአት ዕዳ ተይዞ በሰማያዊ ዳኛ ዘንድ ለፍርድ እንደሚቀርብ ሕሊናው ስለሚወቅሰው የመንፈስ ጭንቀት ይሰማዋል ። ስለዚህ ከኃጢአት ዕዳ ነፃ ለመሆን ስለኃጢአታችን በሞተልን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነንና በንስሐ የኃጢአት ዕዳችንን ከከፈልን ታማኞች እውነተኞች ተብለን ሕይወትነት ያለውን ዘለዓለማዊ ሀብት ለማግኘት ሥልጣን ይኖረናል ። "ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጁዋም ወደከተማይቱ እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው" የሚለውን የሐዋርያውን ቃል ተገንዝበን የኃጢአት ዕዳችንን በንስሐ ከአስወገድን የኃጢአታችንን ዕዳ ለመክፈል በሞተልን በኢየሱስ ክርስቶስ ከአመን ከኃጢአት ዕዳ ነፃ ሆንናል ስማችን በሕይወት መጽሐፍ ስለሚፃፍ ሁለተኛ በኃጢአት ዕዳ ልንያዝ አንችልም ።

መምህር መንክር ፈንታሁን



# ከቋጥኝ ድንጋይ ተፈልፍላ የታነፀችው የደብረ ሲና ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

በቀደምትነቷና በታሪካዊትነቷ የታወቀች ደብረሲና ማርያም ገዳም የምትገኘው በኤርትራ ክፍለ ሀገር (በሰንሒት) አውራጃ ውስጥ ከኢላ ደርዕድ ወደቀኝ በመታጠፍ በእግር የሁለት ሰዓት ያህል መንገድ ከተጓዙ በኋላ የምትገኝ ስትሆን ከአሥመራ ደግሞ እስከ ኢላ በርዕድ ድረስ 70 ኪሎ ሜትር ይሆናል ።

ደብረ ሲና በዓንሳባ ሸለቆ በስተቀኝ በሚገኙት ተራሮች መካከል ከቆላ ቦታ ላይ ካለ አምባ ራስ የምትገኝ ቦታ ናት ።

ልዩ ልዩ ዕፀዋት የሚበቅልባት እንደ መሶብ ቁብ ያለች ናት ለቸርነቱ ወሰን የሌለው ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደ በሁለት ዓመቱ የኢየሩሳሌም ንጉሥ ሄሮድስ ሕፃኑን ኢየሱስን በሰይፍ ሊገለው መፈለጉን እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ስለአወቀች ዮሴፍና ሰሎሜን አስከትላ ሕፃኑን ኢየሱስን አዝላ ስንቃቸውን በአህያ ላይ አስጭና ከሀገሮዋ ከምድረ እስራኤል ተነሥታ ወደ ግብፅ ሀገር ተጉዛ ደብረ ቁስቋም ደርሳ በዚያ በስነበተች ጊዜ ስንቃቸው አልቆባቸው በየ ምደሩ እየዞሩ ቁራሽ እንጀራና ውሃ ሲለምኑ የሚዘከራቸው አጥተው በረኀብና በውሃ ጥም ተሰቃይተዋል ፡

ስለዚህም ጉዳይ ደራሲው አባ ስቆቃወ ድንግል የተባሉ ጻድቅ እመቤታችንን ምን ያህል ችግር እንዳገኛት ሲገልጹ ሚ ዕፁብ ብዝኃ ትህትናኪ ማርያም እግዝእትዩ ምስለ ወልድኪ ባዕለ ዘገብረ ሰማየ ።

ውስተ ደብረ ቁስቋም ኃደርኪ ተመሲለኪ ንዳየ ኢረከብኪ ሰብአ በሀየ ዘይሁበኪ ሲሰየ ወእመ እኮ ለጽምእኪ ማየ ።

= ትርጉም =

እመቤቴ ማርያም ሆይ የትህትናሽ ብዛት ዕፁብ ድንቅ ነው ። ሰማይን ከፈ

www.ethiopianorthodox.org

ጠረ ከባለጸጋው ልጅሽ ጋር ድኃን መስለሽ ደብረ ቁስቋም አደርሽ በዚያ ውም ደግሞ ምግብ የሚሰጥሽ ሰውን አላገኘሽም ለጥምሽም የሚሆን ውሀንም የሚሰጥሽ ሰውን ለማግኘት አልቻልሽም ማለት ነው ። በዚህም ችግርና ሥቃይ እመቤታችን እንደቆየች ልጅዋ ሕፃኑ ኢየሱስ እንግዳ ተቀባዮች የተባረኩና የተመረጡ ሕዝቦች በስተደቡብ እንደሚገኙ ለእናቱ ለድንግል ማርያም በጣቱ አመለከታት እመቤታችን ድንግል ማርያምም ልጅዋ ባመለከታት መሠረት ወደኢትዮጵያ ምድር መጥታ አስቀድመን በርእሱ ከጠቀስናት ደብረ ሲና ደርሳ ዛሬ ቤተ መቅደስ ሆና ከምትቀደስባት ቤተ ክርስቲያን ቋጥኝ ላይ ተቀምጣ ሳለ ሕፃኑ ኢየሱስ ያችን ቋጥኝ ድንጋይ በእጁ ቢዳስሳት በርና መስኮት በተአምር ወጥቶላት ተከፍታ እመቤታችን አይታ ተደነቀች ልጅዋንም አመሰገነች ከዚያች ቋጥኝ ቤትም ግንቦት ፩ ቀን ከተከታዮቿ ጋር ገብተው ተቀመጡ ። በዚያን ዘመን ኢትዮጵያን ይመራ የነበረው ንጉሥ ባዚን ይባል ነበር ንጉሡም እመቤታችን ከልጅዋ ጋር ወደኢትዮጵያ ምድር መጥተው በኤርትራ ደብረ ሲና ውስጥ መቀመጣቸውን በሕልሙ መልአከ እግዚአብሔር ነገረው ንጉሡም በሕልሙ በተነገረው መሠረት ብዙ ሠራዊት አስከትሎ ከአክሱም ወደደብረ ሲና ገሥግሶ ቢደርስ እውነትም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጅዋ ከኢየሱስና ከተከታዮቿ ከሰሎሜና ከዮሴፍ ጋር ከቋጥኝ ድንጋይ በተፈለፈለች ዋሻ ተቀምጠው አገኛቸው ። በግንባሩም ወድቆ ሰገደላቸው ሀገሩም ኢትዮጵያ ክርስቶስን ከእናቱ ጋር ለማስተናገድ እድል ስለገጠማት መንፈሳዊ ደስታ ተሰማው እግዚአብሔርንም አመሰገነ ። ስለክብራቸውም በደብረ ሲና አካባቢ ብዙ የችቦ መብራት አስበራ ከፍ ያለ ግብዣም አደረገላቸው ደብረ ሲና የተባለችይቱንም ቦታ በስላም እንዲተመጡባት መረቀላቸው ። ትም በደብረ ሲና እመቤታችን ማርያም ከልጅዋ ከኢየሱስና ከዘመዶቿ ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር አራት ወራት ከተቀመጡ በኋላ የኢትዮጵያን ምድር ለማዳረስና ለመባረክ በተነሡበት ዕለት ንጉሡ ባዚን ተገኝቶ ብዙ መንፈሳዊ ጨዋታ አንሥተው ከተጨዋወቱ በኋላ እመቤታችን ለንጉሥ ለባዚን እንዲህ ስትል ነገረችው ።

ንጉሥ ሆይ በዚህ በችግሬ ዘመን ለእኔ ያደረግከው ውለታና መስተንግዶ በእኔና በልጄ ዘንድ የማይረሳ ቋሚ ነገር ያለው ነው ። እግዚአብሔር ሀገርህንና መንግሥትህን ይባርክልህ ይህችም የሰነበትኩባት ቦታ የተባረከችና የተቀደሰች ትሁን የቅዱሳን እንጅ የዓለማዊ ቦታ እንዳትሆን ጠብቃት ከብዙ ዘመን በኋላ በስሜ የተሰየመች ታቦት ይገባባታል ታላቅ ገዳም ትሆናለች ። ብዙ መነኮሳት ይቀመጡባታል እኔም በረድኤት አልለያትም ልጄም ጠለ ምሕረቱን አይለይባትም ። ከዚችም ቦታ ከሩቅ መጥቶ ለሚሰግድባትና በቦታዋ ተቀምጦ ደጅ ለጠና ሁሉ በረከተ ሥጋን ፡ በረከተ ነፍስን ያገኛል ። ብላ ባርካ ተሰናበተችው ። ንጉሡ ባዚንም ይህን የመሰለ ታላቅ ተስፋ ከእመቤታችን ስለሰማ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረበ በምድርም ወድቆ ሰገደ ። ያችንም እመቤታችን ከልጅዋ ጋርና ከዘመዶቿ ጋር የሰነበተችባትን የቋጥኝ ድንጋይ ቤት ዙሪያዋን ከልሎ ብዙ ዛፎች እንዲተከሉባት መናንያነ ዓለምም በዚያች ቦታ እንዲቀመጡ አደረገ ።

በዚህ ሁናቴም ብዙ ቅዱሳን እየጸለዩባት ስትኖር በዓጼ ዓላሚዳ ዘመነ መንግሥት አባ ዮሐኒ የተባሉ መነኩሴ ታቦተ ማርያምን ከኢየሩሳሌም አምጥተው ሰኔ ፳፩ ቀን ቅዳሴ ቤቱ ንጉሡ ዓላሚዳና ጳጳሱ አቡነ ናሆም በተገኙበት ተከብሮአል ።

ታቦቷም እንደገባች በእመቤታችን ስም ፈዋሴ ድውያን የሆነ ጸበል ፈልቋል ።
አባ ዮሐኒም በገዳሟ የድንጋይ ጋንና የድንጋይ ወንበር የእንግዳ መቀበያ ክፍል እየቦረቦሩና እየፈለፈሉ ሠርተዋል ገዳሙም የአንድነትና የንፍሮ ገዳም እንዲሆን ደንብ ስለአወጡ ዛሬ ሥርዓቱና ደንቡ እንደጸና ይገኛል ። በየጊዜው የነገሡ ነገሥታትም ዓፄ ባዚን የወሰነውን ደንብ በማክበር በክብር ላይ ክብር እየጨመሩላት ስለኖሩ ዛሬ ይህች ገዳም በንዋየ ቅድሳት በኩል ከፍተኛ ሀብታም ናት በገዳሟ የሚገኘው ንብ ጠላትን እንደጦር ሠራዊት ስለሚያስደነግጠው የጥንት ንዋየ ቅድሳቷ እንደተከበረ ይገኛል ።

የደብረ ሲና ማርያም የቋጥኝ ቤተ መቅደስ በበርዋ ሁለት እግር እንደሌለው ወንበር ትመስላለች አስተውለው ሲመለከቷት መሬት የነካች አትመስልም በስተጀርባ በኩል በዘመናዊ ሕንፃ ለሕንፃዋ መጠባበቂያ ግንብ ተገንብቶአል ሁኔታዋ እንደኳስ ክብ ሁና አራት ሜትር ቁመት ያላት እንደመሶብ ቁብ ያለች አለት ድንጋይ ሁና ቅቧ እንደ ብር እንደ ወርቅ የምታብለጨልጭ ከመሆኗም ሌላ መግቢያው አጠር ጠበብ ያለ ሆኖ ወደ አንድ ዋሻ የሚወስድ ይመስላል ። ውስጡ ግን ለመቅደስ ብቻ የበቃና የሚያገለግል ነው ቅድስትና ቅኔ ማኅሌት ተብሎ ዝቅ ብሎ ከአጠገቧ በግንብ ታንጿል ።

ይህችም የደብረ ሲና ታቦት ለለመናትና ለተማፀናት ሁሉ ፈጥና ሰሚ ከመሆኗ ጋር ብዙ በሽተኞችን የሚፈውስ ጸበልም ስለሚገኝ በጣም የታወቀች ዝነኛ ናት ።

የቋጥኟንም ቤተ መቅደስ ለማየት የታደለ በአንክሮ ፈዞ ይቀራል ።የዚችንም ታሪካዊ ቤተ መቅደስ ታሪክ የያዘው ዜና ድግናዝን ንጉሥ የሚባለው የታሪክ መጽሐፍ ነው ይህም መጽሐፍ ባሕል ሚኒስቴር ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ይገኛል ። በገዳሟ የሚገኙት መነኮሳት በእንግዳ ተቀባይነታቸው የታወቁ መንፈሳውያን ናቸው ።

አንባቢያን ሆይ !

ኢትዮጵያ ሀገራችን ቅርስ ሆና የሚገኝ ባት ይህችን ቤተ ክርስቲያን የመሰለች

ወደ ገጽ ፩ ዞሯል





# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዛመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ሰባት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቁ.
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org